# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ



3ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም / 2021 /

# የክወናና የዕይታ ጥበባት ትምህርት

## የተማሪ መማሪያ መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል


አዘጋጆች

ኤልያስ ደምሴ

እንዳለ አባተ

በላይ አለማየሁ

ኢያሱ ስለሺ

ርብቃ ወንድማገኝ

የማታወርቅ ይታያል

ገምጋሚዎች

ኢየሩሳሌም በዳኔ

ማርቆስ ወልደሐና

ሰሎሞን ኃይለማርያም

አስተባባሪዎች

ጌታቸው ታለማ

ሌይአውት ዲዛይን

በእንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

© 2014ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ጥቅሶችና ሥዕሎች በምንጭነት የተጠቀምንባቸውን ሁሉ እናመሰግናለን።

# ምስጋና

ይህን የትምህርትመጽኃፍ ከዝግጅት ጀምሮ በውጤት እንዲጠናቀቅ፣ የካበተ ልምዳቸውን በማካፈል፣በፓናል ውይይት ሃሳብ በማፍለቅና በማቅረብ፣በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ፣አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ በማድረጋቸው ላደረጉት ከፍተኛ ድጋፍ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ዘላለምሙላቱ የላቀ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

ለስራችን መሳካት ሁልጊዜ አብረውን በመሆን፣በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት፣የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣በመገምገም እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራመሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት ከጎናችንለነበሩ የትምህርት ቢሮየማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ሳምሶንመለሰ፣የትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ፣የትምህርት ቢሮጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ፣የቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታመርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ በመጨረሻም መጽኃፉ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሳነ መምህራን ለስራው ልዩ ትኩረት በመስጠት አዘጋጅ መምህራንን ስለላካችሁልንና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

## ማውጫ

ርዕስ ገፅ

ምዕራፍ አንድ ........ 1
ጥበባዊ ግንዛቤ ........ 1
መለየትና መረዳት ........ 1
1.1 የሙዚቃ መሰረታዊ ኖታዎችን መለየትና መረዳት ........ 2
1.1.1 ከሙሉ የድምፅ ኖታና እረፍት ኖታ እስከ ሩብ የድምፅ ኖታና የእረፍት ኖታ መገንዘብ። ........ 2
1.1.2 ስልተ-ምት (Rhythm) ........ 2
1.1.3 ምት (Beat) ፦ ........ 3
1.1.4 የሙዚቃ ኖታ ድምፃች ........ 3
1.2 ቀላል የሆነ የድራማ ስልቶች ........ 9
1.2.1 ተውኔት ወይም ድራማ ........ 9
1.2.2 ቤት የለሽ ጨዋታ፡ አንድ ........ 10
1.2.3 እኔና ጥላዬ ........ 11
1.2.4 የመዳፍ ጥፊ ........ 12
1.2.5 አገር ........ 12
1.2.6 የአካል ስሞች ........ 13
1.2.7 የምድር ማዕድኖች ........ 14
1.3 መሠረታዊ ቀለማትን መለየትና ማስረዳት ........ 16
1.3.1 ቀላል ፎቶ ግራፍ ........ 18
ማጠቃለያ ........ 19
አጠቃላይ ምዘና ........ 19
ምዕራፍ ሁለት ........ 22
ፈጠራን መግለፅ ........ 22
ተግባራዊ ልምምድ ........ 22
2.1 የድምፅና የእረፍት ምልክቶች ........ 23
2.1.1 ሙሉ ኖታ ........ 24
2.1.2 ሙሉ የእረፍት ኖታ ........ 26
2.1.3 ግማሽ ኖታ ........ 27
2.1.4 ግማሽ ኖታ እረፍት ጊዜ ........ 29
2.1.5 ሩብ ኖታ ........ 30
2.1.6 የሩብ ኖታ የእረፍት ምልክት ........ 31
2.1.7 የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ........ 33
2.2 የዳንስ ተግባራዊ ልምምድ ........ 34
2.2.1 ድርጊታዊ የአንገት በላይ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት ........ 35
2.2.2 መልዕክቶች በድራማ፣ በቪዲዮና በፍቶግራፍ፣ የዳንስን እና የጨዋታ ጭብጦችን መለየት 39
2.2.3 ማስመሰል፣ አከታተብ (imitation) ........ 40
2.2.4 ምን አየሀ? ........ 40
2.2.5 ጓደኛ መፈለግ፣ ........ 41

2.2.6 ጨዋታ የሚወድ ልጅ ........ 41
2.2.7 አንበሳ ........ 43
2.2.8 ፍቅር ........ 44
2.2.9 የፊልም ጥበብ አጀማመር ........ 45
2.4 ቀለል ያሉ ቅርጾች ውጫዊ አካል መሳልና ፎርሞችን ማቅለም ........ 46
2.4.1. ቀለል ያሉ ቅርጾች ውጫዊ አካል መሳል ........ 46
2.4.2 ጂኦሜትሪያዊ ፎርሞች ........ 47
2.4.3 ፎርሞችን ማቅለም ........ 48
2.4.4 መሰረታዊ ቀለማት ቀጥተኛ ህትመት ........ 49
2.4.5 መሰረታዊ ቀለማት ........ 49
2.5.1 መሰረታዊ ቀለማትን ተጠቅመን ቀጥተኛ ህትመት መስራት ........ 50
2.5.2 ማተም ........ 50
2.5.3 በድንች የሚሠራ ህትመት ........ 51
ምዕራፍ ሶስት ........ 53
ባህልን መግለፅ ........ 53
3.1 በብዝሃ ባህል ላይ ያተኮረ ያለፈውና የአሁን የሙዚቃ ጥበብ ........ 55
3.1.2 የክብረ በአላት ዜማዎች:- ........ 56
3.1.3 አምልኮ ዜማዎች:- ........ 60
3.1.4 ለስራ የሚዜሙ ዜማዎች:- ........ 60
3.1.5 ለጦርነት የሚዜሙ ዜማዎች:- ........ 60
3.1.7 ለሃዘን የሚዜም ዜማ:- ........ 61
3.2 አገራዊ ውዝዋዜ ........ 61
3.2 በብዝኃ ባህል ላይ ያተኮረ ያለፈውና የአሁን የትያትር ጥበብ ........ 63
3.3 የድራማ ባህላዊ ገጽታ ........ 64
3.3.1 ታዋቂ ታሪኮች ........ 66
ሀ. ለማ ጉያ ........ 66
ለ. ጥላሁን ገሰሰ (ድምፃዊ) ........ 67
3.4 በብዝሀ ባህል ላይ ያተኮረ ያለፈውና የአሁን የዕይታ ጥበብ ........ 68
3.4.1 የቀለም ባህላዊ ገፅታ ........ 71
3.0.2 የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት: ........ 72
3.4.3 ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት: ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት የምንላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማትን እርስበእርስ በማቀላቀል የምናገኛቸው ሲሆኑ እነዚህም ቀለማት ........ 72
3.4.4 ገለልተኛ ቀለማት:- ........ 73
ማጠቃለያ ........ 75
የማጠቃለያ ምዘና ........ 75
ምዕራፍ አራት ........ 77
ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ) ........ 77
ማድነቅ ........ 77
4.1 የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃን ማድነቅ ........ 78

4.1.1 ለብዙ ዘመናት ከውጭ ሀገር ተፅእኖ ስር ያልወደቀ መሆኑ ........ 79
4.1.2 በተለያዩ አካባቢ ብዙ አይነት የሙዚቃ ባህል መኖራቸው ........ 79
4.1.3 በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች መኖራቸው ........ 79
4.1.4 ለተለያዩ አላማዎች መዜማቸው ........ 80
4.1.5 ከማህበረሰቡ ጋር ጥብቅ ትስስርና ቁርኝት ያለው መሆኑ ........ 80
4.1.6 ለሃገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገሮች እንደመለያ አርማ የሚያገለግል መሆኑ ........ 80
4.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ የውዝዋዜ ጥበብ ........ 84
4.3 የኢትዮጵያ ባህላዊ ትያትርን ማድነቅ ........ 86
4.3.1 የኢትዮጵያ ባህላዊ የክወና ጥበባት ........ 87
4.3.2 እኔ ነኝ ውሮ ........ 88
4.4 የኢትዮጵያ ባህላዊ የዕይታ ጥበብ ........ 44
4.4.1 ቀለም ቅብ ........ 90
4.4.2 ኪነ-ሕንፃ ........ 92
4.4.3 የዕደ ጥበብ እና የጌጣጌጥ ውጤቶች ........ 93
ማጠቃለያ ........ 94
ማጠቃለያ ምዘና ........ 95
ምዕራፍ አምስት ........ 96
ጥመርታ ዝምድናና፣ ትግበራ ........ 96
የቡድን ስራ ........ 96
5.1 ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና ........ 97
5.1.1 የሙዚቃ ትምህርት ከአካባቢ ሳይንስ ጋር፡- ........ 98
5.1.2 ሙዚቃ ከቋንቋ ትምህርቶች ጋር፡- ........ 99
5.1.3 ሙዚቃ ከኤሌክትሮኒክስና ኤሌክትሪሲቲ ጋር፡- ........ 99
5.1.4 ለእርስ በራስ ግንነኙነት፡- ........ 99
5.1.5 ሙዚቃ ከታሪክ ትምህርት ጋር፡- ሙዚቃ ከታሪክ ትምህርት ጋር ጥብቅ ግንኙነት አለው፡ ፡ ........ 100
5.2 የውዝዋዜ ጥበብ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ዝምድና ........ 102
5.2.1 እፅዋትን መግለፅ ........ 104
5.3 የትያትር ጥበብ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና ........ 105

5.4 የዕይታ ጥበብ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና ........ 106
5.4.1 የዕይታ ጥበብ ከአካባቢ ሳይንስ አንፃር ........ 106
ማጠቃለያ ........ 109
የማጠቃለያ ምዘና ........ 110
ዋቢ መፃህፍት ........ 111

# ምዕራፍ አንድ

## ጥበባዊ ግንዛቤ

### *መለየትና መረዳት*

### *መግቢያ*

ጥበባዊ ግንዛቤ ተማሪዎች አብረው ከሌሎች ትምህርቶች በእኩል ሊያዳብሩት ይገባል፡፡ በመሆኑም በአካባቢያችን የምናያቸውን፣ የምንሰማቸውን፣ የምንዳስሳቸውን ጥበባዊ ክዋኔዎች በጥልቀት መረዳት እንድንችል በየጊዜው መሞከርና በትምህርት መደገፍ አስፈላጊ ነው፡፡

**የትምህርቱ አጠቃላይ አላማ**

ይህንን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የሙዚቃ ኖታዎችን ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነ እረፍት ምልክታቸው ትለያላችሁ፡፡
- መሠረታዊ ቀለማትን ትለያላችሁ
- ቀላል የፎቶግራፍ ዘዴዎችን ትለያላችሁ፡፡
- ቀላል የድራማ አሰራር ዘዴን ትለያላችሁ፡፡

## 1.1 የሙዚቃ መሰረታዊ ኖታዎችን መለየትና መረዳት

ከዚህ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች መሰረታዊ የሆኑ የሙዚቃ ኖታ (ምልክቶችን) በቀላሉ ለይታችሁ ትረዳላችሁ፡፡ እያንዳንዱን መሰረታዊ ምልክቶች ደጋግሞ በማየት የሚኖራቸውን የድምፅ ውክልና እንድትገነዘቡ ያስችላችኋል፡፡

**የዚህ ትምህርት አጠቃላይ አላማ:-**

1.1.1 ከሙሉ የድምፅ ኖታና እረፍት ኖታ እስከ ሩብ የድምፅ ኖታና የእረፍት ኖታ መገንዘብ፡፡

የሙዚቃ ኖታ (ምልክቶች) ራሳቸውን የቻለ ቅርጽና የሚወክሉት ምትና ድምፅ አላቸው፡፡ እነዚህን ምልክቶች በሂደት በመለማመድ የሚለመድ በመሆኑ ደጋግማችሁ በመመልከት የሙዚቃ ፅሁፍን ማንበብና መፃፍ ትችላላችሁ፡፡

### 1.1.2 ስልተ-ምት (Rhythm)

- ስልተ-ምት በሙዚቃ ውስጥ ድምፆች በጆሯችን ስንሰማቸው አንድ ጊዜ ጠንከር አንድ ጊዜ ላላ የሚል ስሜትን የሚሰጡ የድምፆች ፍሰት ነው፡፡
- ስልተ-ምት ማለት በሙዚቃ ውስጥ በጣም አስፈላጊ የሆነ የሙዚቃ ክፍል ነው፡፡
- ይህ የሙዚቃ ዋና የጀርባ አጥንት ነው፡፡
- ኖታ የሙዚቃን ድምፆች የጊዜ ቆይታ ማለትም መርዘም እና ማጠር ፡፡
- ምት ማሳያ ምልክቶች በርካታ ቢሆኑም የተወሰኑትን ብቻ እናያለን፡፡
- እነዚህ የሙዚቃ አፃፃፍ ስልተ-ምት የምንማራቸው ምልክቶች ድምፅንና ምት ሊወክሉ ይችላሉ፡፡

### 1.1.3 ምት (Beat) ፡-

ምት ማለት ተከታታይነት እና እኩል የሆነ የነገሮች እንቅስቃሴ፡ነው፡፡ የሙዚቃን ምት ስንሰማ ከታች ደርሶ የሚመለስ ምት የሚል ድምፅ የምንሰማው ም ይባላል፡፡

- በቀላሉ ምትን ለመረዳት ልባችንን በእጃችን ተጭነን ስንይዝ የልባችንን ደም መርጨት እጃችን ላይ ይታወቀናል፡፡ ይህ የልብ ምት ይባላል፡፡ የሙዚቃ ምትም እንደዚሁ አይነት ተከታታይ ስሜት ይሰጠናል፡፡

- የሰዓት የሰኮንድ አቆጣጠር ቋሚ አይነት ቲክ፤ቲክ፤ቲክ፤ቲክ የሚለውን ድምፅ እንደ ምት መቁጠር እንችላለን፡፡

- የሰዎች እርምጃ አንድ አይነት ፍጥነት ያለው እርምጃ ሲራመዱ ቋ፤ቋ፤ቋ፤ቋ የሚለውን ድምፅ እንደ ምት ማሰብ እንችላለን፡፡

- ምት የሙዚቃን ወይም የመዝሙሩን አካሄድ እኩል በሆነ ፍጥነት ያስኬደዋል፡፡

- አንድ ምት ማለት አንድ ጊዜ ደርሶ የሚመለስ የግዜ ቆይታ ማለት ነው፡፡

### 1.1.4 የሙዚቃ ኖታ ድምፆች

ሙዚቃን ለመፃፍ ብዙ የኖታ አይነት ምልክቶች ሲኖሩ በዚህ ትምህርት ውስጥ ጥቂቶቹን ብቻ የምናይ ይሆናል፡፡

#### የሙሉ ኖታ ምልክት

ሙሉ ኖታ ከሙዚቃ ምቶች መካከል የመጀመሪያውና ትልቅ የጊዜ ቆይታን የሚገለፅበት የኖታ ዓይነት ነው፡፡

- ሙሉ ኖታ አራት ምት አለው፡፡ ይህም ማለት አራት ጊዜ እግር 4ግዜ ከታች ደርሶ ሰየመመለስ ግዜ አለው፡፡
- ምልክቱም ሞላላ ክብ ቅርፅ ነው፡፡



ምስል 1፡- ሙሉ ኖታ

- ሙሉ ኖታን ከፀሐይ እና ከጨረቃ ክብነት ጋር ማዛመድ እንችላለን፡፡
- ክብ የሆነ ነገርን በመጠቀም ሙሉ ኖታን መገንዘብ እንችላለን፡፡




ምስል 2፡- ሙሉ ምት ከነ አራት ምት አቆጣጠር

## መልመጃ 1

የሚከተለውን ሙሉ ምት ኖታ በመደጋገም ተለማመዷቸው፡፡




### የሙሉ ኖታ እረፍት ምልክት

ይህ የሙዚቃ ኖታ የሙሉ ኖታ አቻ እረፍት ጊዜ ዋጋ ያለው ነው፡፡ አራት ምት ሙሉ ዝም በማለት ቆጥረው ማሳለፍ ነው፡፡

- ሙሉ እረፍት የራሱ ምልክት አለው፡፡
  አራት ጊዜ እስከምንቆጥር ድረስ እረፍት መውሰድ ነው፡፡



ምስል 3፡- ሙሉ እረፍት ምልክት

- ሙሉ እረፍት ምልክትን በተገለበጠ ኮፍያ (ቆብ) አምሳያ ማሰብና ማስታወስ እንችላለን፡፡
- ሙሉ እረፍት ሙዚቃ ውስጥ ብቻውን ሁልጊዜ የሚመጣ ብቻ ሳይሆን ከሙሉ ኖታና ከሌሎች ኖታዎች ጋር በመፈራረቅ ይመጣሉ፡፡




ምስል 4፡- የሙሉ ኖታና ሙሉ እረፍት

## የግማሽ ኖታ ምልክት

የግማሽ ኖታ ምልክት የሙሉ ኖታ ግማሽ ያክል ዋጋ ያለው ነው፡፡

- ግማሽ ኖታ ምልክት ሁለት ምት ያክል ይቆያል፡፡ (ሁለት ጊዜ በእኩል ደርሰው ማሰብ እንችላለን)
- ግማሽ ምት የራሱ የሆነ ምልክት አለው፡፡
- ሞላላ ክብ ቅርፅ በስተግራው ወደታች ወይም በስተቀኝ ወደላይ ከክቡ ጋር ተገናኝቶ የሚሰመር ቀጥታ መስመር አለው፡፡
- ወደላይ ወይም ወደታች ቢሰመርም አንድ አይነት ናቸው፡፡




ምስል 5፡- ግማሽ ኖታ ምልክት

## የሩብ እረፍት ምልክት

የግማሽ ኖታ እረፍት ምልክት እንደ ግማሽ ኖታ እኩል የጊዜ ዋጋ አለው፡፡

- የግማሽ ኖታ እረፍት ምልክት ለሁለት ተከታታይ ምቶች በዝምታ (ድምጽ ባለማውጣት) መቆየት ማለት ነው፡፡

- ግማሽ ኖታ ላይ ሁለት ከታች ደርሶ የሚመለስ ምት ሚሉ ድምጾችን እስከምንሰማ ድረስ እንደምንቆጥረው ሁሉ የግማሽ እረፍት ምልክትም እነዚህን ጊዜአት ዝም በማለት እናሳልፋለን ማለት ነው፡፡
- ይሄም ምልክት ከሌሎች ምልክቶች ጋር አንድ ላይ በመደበላለቅ ሊጻፍ ይችላል፡፡
- ግምሽ እረፍት ኖታን በኮፍያ (በቆብ) አምሳያ ማስታወስ እንችላለን፡፡



ምስል 6፡- የግማሽ ኖት እረፍት ኖታ (ምልክት)

መልመጃ 2፡- የሚከተሉትን ምልክቶች በመደጋገም ፃፉ፡፡



## የሩብ ኖታ ምልክት

ሩብ ኖታ የሙሉ ኖታ አንድ አራተኛ ዋጋ ያለው ሲሆን የግማሽ ኖታን ደግሞ አንድ ሁለተኛ ዋጋ ያለው ነው፡፡

- ይህ ሩብ ኖታ ሞላላ የጠቆረ ክብ እና ከግራ በኩል ወደ ታች እና ከቀኝ በኩል ወደላይ የሚሰመር ቀጥ ያለ መስመር ያለው ነው፡፡
- ጥቁር ክቡ ወደላይ ወይም ወደታች ሊሆን ይችላል፡፡



ወይም



ምስል 7፡- ሩብ ኖታ

- እያንዳንዱ ሩብ ምት አንድ ድው የሚል ምት ወይም አንድ የልብ ምትን ይመስልልናል፡፡
- በእጃችን ስናጨበጭብ እያንዳነዱን ጭብጨባ በሩብ ምት ኖታ መወከል እንችላለን፡፡

## ሩብ ኖታ እረፍት ምልክት

ሩብ ምት እረፍት ኖታ ምልክት ከሩብ ኖታ ጋር እኩል ዋጋ አለው፡

- እያንዳንዱ ሩብ ኖታ እረፍት ምልክት አንድ ልብ ምት፣ አንድ ጭብጨባ ያክል የጊዜ ቆይታ ያለው፡፡
- የራሱ የሆነ ቅርፅ ያለው ምልክት አለው፡፡



ምስል 8፡- ሩብ እረፍት ኖታ




ምስል 6፡- ሩብ ኖታ ከእኩያው ከሩብ እረፍት ኖታ ጋር

መልመጃ 3፡- የሚከተሉትን ኖታዎች በመፃፍ ተለማመዱ፡፡



- ማንኛውም የሙዚቃ ኖታ ሊፈራረቅ ይችላል፡፡

## 1.2 ቀላል የሆነ የድራማ ስልቶች

ኪነ-ጥበብማለት የስዕል፣የቅርጽን፣የጽሑፍን እንዲሁም የሙዚቃን ሙያዎች ያካተተ የትምህርት ዘርፍ ነው ብለናል፡፡ኪነጥበብ የሰው ልጅ ገጠመኝ መከሰቻ በመሆናቸው አንድነት አላቸውና ሥነጽሁፍን ወይም ተውኔት/ድራማ፣ ሙዚቃ፣ ስዕል እና ቅርጻ ቅርጽ ባጠቃላይ ኪነ-ጥበብ ብለን እንጠራቸዋለን፡፡

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-**

- የድራማ ስልቶችን ትረዳላችሁ፡፡
- የድራማ ምንነት ትለያላችሁ፡፡
- ተረቶችን በድራማ መልክ በመተረክ ታቀርባላችሁ፡፡

### 1.2.1 ተውኔት ወይም ድራማ

ተውኔት ወይም ድራማ ለመዝናናት ፋይዳ ሲባል የሌሎችን ባሕርይ ሁናቴና ንግግር ለጊዜው ወርሶ ክዋኔን ከቋንቋ ጋር አገናኝቶ መጫወት ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ከቤተ-ተውኔት ውጭ ሊተወን ቢችልስ ማን ከልካይ አለበት?

ከዚህ አኳያ ተነስተን የልጆችን ዕቃቃ ጨዋታዎች፣ባህላዊ ስርዓቶች፣ሃይማኖታ ዊ ክንዋኔዎችን፣ የመሳሰሉትን ሁሉ "ነገረተውኔት" ወይም የተውኔት ገጽታ እንዳላቸው ልንገነዘብ ይገባል፡፡

ስለዚህ ተውኔት በሁለት መንገዶች ይከወናል የመጀመሪያው ህዝባዊ ወይም በማህበረሰቡ የሚከወኑ፣ያልተወሳሰቡ ወይም መደበኛ ቦታ የሌላቸው ሲሆኑ፣ሁለተኛው ደግሞ በቤተ ተውኔት የሚከወኑ የተወሳሰበ ባህሪይ እና ሴራ ያላቸው ናቸው፡፡ የመጀመሪያውን አይነት ህዝባዊ ወይም ማህበረሰባዊ የሆነውን የድራማ አይነት በዚህ ክፍል እንመለከታለን፡ ፡

- ስለ ሰውነት ክፍሎች
- ስለ ተፈጥሮ
- ስለ ሳይንስ
- ዕቃቃ ጨዋታዎች፣ ባህላዊ ስርዓቶች ወዘተ----
- ተረቶች በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ማድረግ፡ ፡

ከዚህ በመቀጠል ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን በተለያየ መልኩ እንመልከት፦

### 1.2 .2 ቤት የለሽ ጨዋታ አንድ

በዚህ ጨዋታ ልጆች አይቶና ሰምቶ በተግባር የመግለፅ ችሎታችሁን ታዳብሩበታላችሁ እንዲሁም ንቃት እና ቅልጥፍና እንዲኖራችሁ

ያግዛል፡ ፡

ስዕል 1፡-



የጨዋታው ህግ ፦ ከተቀመጡት ዘጠኝ ትናንሽ ክቦች ውጭ አስር ልጆች እንዲቆሙ ማድረግ በ መቀጠል መምህሩ ትዕዛዝ ሲሰጥ ውጪውን ወይም ዙሪያውን ልጆች ይሮጣሉ በመቀጠል "ቁም በቤትህ" ሲል መምህሩ በእያንዳዱ ትንሽ ክብ ውስጥ ይቆማሉ፡፡ የመቆሚያ ቦታ ያጣ ልጅ ከጨዋታው ይወጣል በዚህ አካሄድ እስከ መጨረሻው አሸናፊ ድረስ ጨዋታው ይቀጥላል ፡፡

### 1.2.3 እኔና ጥላዬ ጨዋታ ሁለት

ሁለት ልጆች ፊትና ከኋላ በመሆን የፊተኛው ልጅ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ የኋለኛው ልጅ እንደ ጥላ በመሆን እሱ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በማስመሰል መከወን ወይም ማድረግ፡፡

ስዕል 2



በዚህ መሰረት የተለያዩ አይነት አንቅስቃሴዎችን በማድረግ ለመምህራችሁ አሳዩ፡ ፡

### 1.2.4 የመዳፍ ጥፊ ጨዋታ ሶስት

የመዳፍ ጥፊ ጨዋታ የማሰብ ችሎታን ለማደበር እና በቅልጥፍና ያለስህተት መስራት ጊዜን እንደሚቆጥብ ያስገነዝባል፡፡

በሁለት እኩል ረድፍ በመሰለፍ በመቀራረብ በቁመት እና በሰውነት እኩል የሆኑ ልጆች ፊት ለፊት ትይዩ ተጠጋግቶ በመቆም ጨዋታውን ለመጀመር መምህራችሁ ምልክት ሲሰጥ እያንዳዱ ልጅ ለብቻው ሶስት ጊዜ ያጨበጭብና እጆቹን በደረት ከፍታ በማንሳት ፊት ለፊት ከ ፓደኛው ጋር በማጨብጨብ ሁኔታ ማገናኘት፤ ከዚያም በማውረድ አንድ ግዜ ብቻ በማጨብጨብ የግራ እጆቻችሁን ማገናኘት፡ ፡ በዚህ ሂደት እንደገና ሶስት ሶስት ጊዜ በማጨብጨብ መጀመር፡ ፡ ምንም ስህተት ያልሰራ ወይም ትንሽ ስህተት የሰራ የጨዋታው አሸናፊ ይሆናል፡ ፡



ስልዕ 3

ቀጥሎ የቀረበውን የክቡር ከበደ ሚካኤል አገር የተሰኘ ስንኝ ተለማምዳችሁ ለመምህራችሁ በድራማ መልክ በመተረክ አቅርቡ፤

## 1.2.5 አገር

አገር በታሪክ በቋንቋ በሃይማኖት በልማድ በተስፋ በደስታና በመከራ ተሳስሮ የሚኖር አንድ ወገን የሆነ ሕዝብ የሚኖርበት የዓለም ክፍል ነው።

አገር ማለት አያት ቅድመ አያት የተወለዱበት አድገውም በጀግንነት ከውጭ ጠላት እየተከላከሉ ለሕዝብና ለመንግሥት የሚጠቅም ሥራ ሠርተው

ዕድሜያቸው ሲደርስም ልጆቻቸውን ተክተው የተቀበሩበት ጉድጓድ ነው፡፡

በመወለድ እትብት በመሞት አካል ከአፈሩ ጋር ስለ ሚዋሐድ፣ የአገሩ አፈር ሕዝቡ በላዩ የሚኖርበት ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔር ከምድርዋ ፍሬ ሕይወት እንዲገኝባት በማድረጉ አገር እያጠባች የምታሳድግ ፍቅርዋ በአጥንት በሥጋ ገብቶ የማይደመሰስ የሆነች እናት ማለት ነው፡፡

ከልጅነት ጀምሮ ወንዙን ተራራውን ሜዳውን ቆላውንና ደጋውን በማየት ስለ ማደግ አባቶች በሕይወትና በሞት የሠሩበት ደግ ሥራ በአእምሮ ታትሞ ስለ ቀረ በአገር እስካሉ ሲታይ፤ በስደት ሲሆን ሲታሰብ ፍቅርና ናፍቆት የሚያሳድር አገር ነው፡፡

አገር አባት እናት ዘመድ ምግብ ጌጥና ሀብት በመሆኑ፤ ድኽነትና ጥቃት በመጣ ቁጥር እስከ ሞት ድረስ እንዲሠራበት ከአያት ከቅድም አያትና ከአባቶች በጥብቅ የተሰጠ ያደረ ገንዘብ ነው፡፡

ቀጥሎ የቀረበውን የክቡር ከበደ ሚካኤልን የአካል ስሞች ስንኝ ተለማምዳችሁ ለ መምህራችሁ አቅርቡ፡ ፡

### 1.2.6 የሰው አካል ስሞች

እኔ አንድ ልጅ ነኝ፡፡ የማስብበት ራስ አለኝ፡፡ የማይባቸው ሁለት ዐይኖች የምሰማባቸው ሁለት ዦሮዎች የማሸትበት አፍንጫ የምበላበት አፍ አሉኝ፡፡

ባፌ ውስጥ የምናገርበት ምላስ የምነክስበት ጥርስ አፌንም የምዘጋባቸው ከንፈሮች አሉኝ፡፡

በራሴ ጠጉር ይበቅላል፡፡ ሁለት ክንዶች አሉኝ ጥርስ አፌንም የምዘጋባቸው ከንፈሮች አሉኝ፡፡

በራሴ ጠጉር ይበቅላል። ሁለት ክንዶች አሉኝ። በክንዶቹም ጫፍ እጅ፤ በእጇም ላይ አንድ (መንኮብ) አውራጣት አራት ጣቶች በጣቶችም ጫፍ ጥፍር አለ።

በእጆቼም ብዙ ነገር ማድረግ እችላለሁ። ደግሞ ለመራመድና ለመዝለል ሁለት ቅልጥሞችና ሁለት እግሮች አሉኝ፤ በያንዳንዱ እግር አምስት ጣቶች፤ በያንዳንዱም ጣት አንዳንድ ጥፍሮች አሉ።

ሁሉን ማድረግ እችልባቸዋለሁ እንጂ የብልቶችንና የአካላትን ስም መናገር አልችልም። ፈጣሪ እንዲጠቅሙኝ ብሎ ። አካላትን ሰጥቶኛልና ሰውነቴን ንፁሕ ማድረግ ይገባኛል።

ቆዳና ሥጋም አለበስከኝ ባጥንትና በጅማትም አጸናኸኝ።

አንተ ምንድን ነህ ?

እንዴትስ ሆነህ ተፈጥረሃል?

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን የክቡር ከበደ ሚካኤልን ስንኝ ስለ ማዕድናት ሁኔታ እና አፈጣጠር እና ጥቅም ተለማምዳችሁ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡ ፡

### 1.2.7 የምድር ማዕድኖች

ማዕድኖች አንዳንድ ጊዜ እንዲያው ነጥረው ይገኛሉ። ሌላም ጊዜ ከአፈር ወይም ከድንጋይ ወይም ከሌላ ማዕድን ጋራ ተደባልቀው ይገኛሉ። ከነዚህም የሚለዩት በማጠብ በመውቀጥ በማቃጠል ነው።

ወርቅ ብሩህና ብጫ ከባድና ለስላሳ ነው። በአውስትሪያሊያ በአፍቃና በደቡብ አሜሪካ በብዙ ቦታዎች ይገኛል።ወርቅ የሚገኝበት አካባቢ የወርቅ ማውጫ ይበላል በአብዛኛው ጥቃቅን ሆኖ ይገኛል። አንዳንድ ጊዜም እየተድበለበለ ይወጣል።

አንዳንድ ጊዜም እንደ ክር በቀጭኑ ረጅም ሁኖ ይገኛል። ወርቅ ወንዝ ለወንዝ በአሸዋ ላይ ተሞልቶ ይገኛል። የወርቅ ዋጋው ከማዕድናት ሁሉ ይበዛል። ይልቁንም ጌጥና ገንዘብ ሆኖ ይሠራል። ቀለበት ድሪ፤ ጉትቻ፣ ጽዋ፤ አምባር ይህ ሁሉ ከወርቅ ይሠራል።

ብር እንደ ወርቅ አይደለም እንጂ ብሩህና ከባድ ነው፡፡ በአሜሪካ በብዙ ይገኛል፡፡ ዋጋውም ከወርቅ ቀጥሎ ይገመታል፡፡ ጌጥና ገንዘብ እየሆነም ይሠራል፡፡ በኢትዮጵያ ዋና ገንዘባችን ወርቅና ብር ነው፡፡ ብር አንድ ሩብ እንድ ሩብ መሐለቅ እየሆነ ይሠራል፡፡ ሣንቲም ግን ከነሐስ ነው፡፡ ደግሞ ወለባ ጉትቻ ቀለበት፤ድሪ፤ሰንሰለት፤የሰንጢ እጀታ፤ሹካ፤ማንኪያ፤ጉብጉብ፤ የፈረሰ ቤነቻ ቢላዋ አምባር ሜዳልያ ይኸን የመሰለ ነገር ሁሉ ከብረት ይሠራል፡፡

እርሳስ መልኩ ደበስ ያለ ብልጭልጭታ ያለው ከማዕድናቱ ሁሉ የለሰለሰ ነው፡፡ በእንግሊዝ ደሴቶች በልዩ ልዩ ክፍሏ በዓለምም ባንዳንድ ስፍራ ይገኛል፡፡ እርሳስ ከማዕድናቱ የተለመደና የታወቀ ነው፡፡ እጅግ ለስላሳ በመሆኑ እንዳደረጉት ሆኖ ለመስራት ይመቻል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያንና ለቤት ክዳን ይጠቅማል ለውሃ ፓምፕና ለበርሜልም ይሆናል፡፡

ብረት ጠቆር ያለ ዐይነት ነው፡፡ ብርቱና ተሰባሪ ነው፡፡ ከእንግሊዝ አገር ብዙ ይወጣል፡፡ ብረት ብዙ ጥቅም ያለው የታወቀ ማዕድን ለንግድ ሁሉ የሚያስፈልግ ነው፡፡ መርከቦች መኪና ቤተ ክርስቲያን የሠረገላ ዐይነት ሁሉ ትልቅም ሆነ ትንሽ ሲሰራ ብረት ያስፈልገዋል፡፡ ከወርቅና ክብር ገንዘባችንን እንሠራለን፡፡ ዕዳችንንም እንከፍላለን፤ ሰውነታችንን እናስጌጣለን፡፡

ከብረት መሳሪያችንን እንሰራለን፡፡ ስለ ሀገራችንም እንመለከትበታለን ብዙ የችግራችንንም ቀዳዳ፤ እንደፍንበታለን፡፡ ከ ብረት ወርቅና ብር እንደ እንግሊዝ ሀገር በኢትዮጵያም ይሚገኝ ይመስላችኋል? ያለበትን ስፍራ ለማወቅ ትችላላችሁን?

## 2.7 መልመጃ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ስህተት ከከሆነ ደግሞ ሀሰት መልሱ፡፡

1. ተውኔት ከምናባዊ ሥነ-ጽሁፍ ይመደባል፡፡
2. ተውኔት ከኪነ-ጥበብ ዘርፎች አንዱነው፡፡
3. ሙዚቃ፣ ቅርፃቅርፅ፣ ስእል እና ተውኔት ከኪነጥበብ ዘርፎች ይመደባሉ፡፡
4. ተውኔት ከሰው ልጆ እውነተኛ ድርጊት የሚከተቡ የኪነ-ጥበብ ዘርፎች አይደለም፡፡

### የግንዛቤ ጥያቄዎች

1. ልጆች ስለ ማዕድናት ምን ተረዳችሁ?
2. ስለ ሰውነት ክፍሎችስ ምን ተረዳችሁ?
3. በተጫወታችሁዋቸው ልዩ ልዩ ጨዋታዎች ምን ተረዳችሁ?

## 1.3 መሠረታዊ ቀለማትን መለየትና ማስረዳት

### የትምህርቱ ዝርዝር አላማ

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኃላ
- መሰረታዊ ቀለማትን ታውቃላችሁ
- ቀለማት በአካባቢያችን የት እንደሚገኙ ትገነዘባላችሁ
- ከፎቶ ግራፍ ምስሎችን ትለያላችሁ
- ስዕሎችን ትስላላችሁ

- መሰረታዊ ቀለማት ማለት የትኛውም ቀለም ተቀላቅሎ የማይፈጥራቸው ናቸው
- መሰረታዊ ቀለማት ሌሎች ተጨማሪ ቀለማት እንድናገኝ ይረዱናል

- መሰረታዊ ቀለማት የምንላቸው ሰማያዊ፣ ቀይ እና ቢጫ ናቸው

ምስል 1



ሰማያዊ ቀይ ቢጫ

መሠረታዊ ቀለማት አይነት ያላቸውን ምስሎች

ለምሳሌ ሠማያዊ በሠማይ፣ በአዕዋፋት በአበቦች ወ.ዘ.ተ ይገኛል

ምስል 2



ቀይ ቀለም እንደ ሠማያዊ ሁሉ በተፈጥሮ ላይ ልናገኘው እንችላለን ለምሳሌ በአበቦች፣ በአዕዋፋት፣ በእሳተ ጎመራ ወዘተ ይገኛል

ምስል 3




ቢጫ ቀለም ከመሠረታዊ ቀለማት አንዱ ሲሆን በተፈጥሮ ላይ በአዕዋፍ፣ በአበቦች ወዘተ እናገኝዋለን

ምስል 4




## 1.3.1 ቀላል ፎቶ ግራፍ

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኃላ የተለያዩ ፎቶግራፎች በመመልከት ምሳሌዎች በቀላሉ እንድታስታውሱት የፎቶግራፍ ጥቅም በጥቂት ትረዳላችሁ ፎቶግራፍ ከጥበብ ስራዎች አንዱ ሲሆን መልእክቶችን ለማስተላለፍ ይረዳናል፣ የፎቶግራፍ ጥቅም እጅግ ብዙ ሲሆን በየእለቱ ህይወታችን ላይ የሚገኙ ሆኖ እናገኝዋለን፣ በመንገድ ላይ የምታዩዋቸውን የተለያዩ ማስታወቂያዎች ፣ምስሎች ፣በቤታችን ግርግዳ ወይም የፎቶ አልበም ላይ የምታዩዋቸው የተለያዩ ፎቶግራፎች የሰውን የኗላ ገጽታ የሀገራችን ባህል፣ በተለያየ አለም ላይ ያሉ ድንቃድንቅ ታሪኮችን በቀላሉ በቤታችን በአካባቢያችን በፎቶግራፍ አማካኝነት እናገኛለን፡፡

## የተግባር ጥያቄ

1. ተማሪዎች በደብተራችሁ መሰረታዊ ቀለማትን ቀላቅላችሁ ቀቡ?
2. የተለያዩ ፎቶግራፎችን በማየት ስለፎቶ ተናገሩ?
3. መሰረታዊ ቀለማትን ብቻ በመጠቀም ስዕሎች ሣሉ?

### ማጠቃለያ

ከላይ በዝርዝር የተቀመጡትን ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነ አቻ እረፍት ምልክታቸው በቅርፃቸውና በጊዜ ቆይታቸው አይታችኋል፡፡ በተማራችሁት መሰረት በትኩረት እንድትለዩና እንድትለማመዱ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በምዕራፍ አንድ የዕይታ ጥበብ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ስለመሰረታዊ ቀለማት በምስል፣ በተለያዩ ምሳሌዎች አውቀዋል ቀለል ባሉ ፎቶግራፎች ደግሞ ምስሎችን ምንነት አውቀዋል፡፡

## አጠቃላይ ምዘና

1.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በተገቢው ቦታ መልሱ፡፡

1. ከሚከተሉት ወስጥ ሙሉ ኖታ ምልክት የቱ ነው




2. ሙሉ ኖታና ግማሽ ኖታ አንድ አይነት ምልክት አላቸው፡፡

ሀ. እውነት　　　　ሐ. ሀ ና ለ

ለ. ሐሰት　　　　መ. መልስ የለውም/አልተሰጠም/

3. ከሚከተሉት ውስጥ የሩብ ኖታ ውክልና ያለው የቱ ነው

ሀ. 
ሐ. 

ለ. 
መ. 

የሚከተሉትን ምልክቶች በማስመር አዛምዱ



1. ሩብ ኖታ



2. ግማሽ ኖታ



3. ሩብ እረፍት ኖታ



4. ሙሉ እረፍት ኖታ



5. ግማሽ እረፍት ኖታ



6. ሙሉ ኖታ

3.ከዚህ በታች ለተቀመጡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ

1. መሠረታዊ ቀለማትን ደብተራችሁ ላይ ስዕል ስላችሁ በመቀባት አሳዩ?
2. መሰረታዊ ቀለማት ምን ምን ናቸው ሶስቱን ጥቀሱ?

ሀ. ________________

ለ. ________________

ሐ. ________________

3. ቢጫ ቀለምን በተፈጥሮ ላይ የት ልናገኘው እንችላለን ?____________

__________________________

4. ከዚህ በታች የምንመለከታቸው ፎቶግራፎች ማንነት ጻፉ?



-------------------------------------------------------

5. 


-------------------------------------------------------

4.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት/ ስህተት ከሆነ /ሐሰት ብላችሁ መልሱ፡፡

1. መሰረታዊ ቀለማት የምንላቸው ቀይ ቢጫና አረንጓዴ ናቸው? --------
2. ሠማያዊ ቀለም በአደይ አበባ ላይ ይገኛል? -------------------------
3. መሰረታዊ ቀለማት በተፈጥሮ ላይ ሊገኙ ይችላሉ? -----------------

# ምዕራፍ ሁለት

## ፈጠራን መግለፅ

### ተግባራዊ ልምምድ

### መግቢያ

በክፍለ ትምህርት አንድ በጥበባዊ ግንዛቤ መለየት እና ማስረዳት በሙዚቃ፤ በስዕል፤ እና በትያትር፡ የድምፅ ኖታና የእረፍት ኖታ እስከ ሩብ ኖታ የድምፅ ኖታና የእረፍት ኖታ፡ መሰረታዊ የሆኑ ቀለማት በስዕል እና ቀላል የድራማ ዘዴዎች እንደተማራችሁ ይታወቃል። በዚህ በክፍል ሁለት ደግሞ ፈጠራን የመግለፅ ተግባራዊ ልምምድ የምንመለከት ይሆናል።

### የትምህርቱ አጠቃላይ አላማ

ይህንን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- በድምፅና በምስል የሚያዩዋቸውንና የሚሰሟቸውን መልዕክቶችን ምስሎችን ድርጊቶችን ትለያላችሁ።
- ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነእረፍት ኖታቸው በቀላል የምት መሳሪያዎች ተጫውተው ትለያላችሁ።
- የቤተሰባዊ ሚናዎችን በመዘመር፣ በውዝዋዜ በሚና ጨዋታ በማስመሰል ትለያላችሁ።
  - ሥዕሎችን ስሎ ማሳየት፣ ቀለማትን መደባለቅ ማተምና መቀባት

ማንኛውም ሙያ እንደሚያስፈልገው አይነት ተግባራዊ ልምምድ ይፈልጋል፡፡ በተለይም ደግሞ ሙዚቃ ለተግባራዊ መለማመጃ ጊዜ እና ቦታ መርጦ በመደጋገም መለማመድን ይጠይቃል፡፡ ተግባራዊ ልምምድ ሙዚቃን ለመረዳትና በተግባር ለመጫወት የሚያሰችል ወሳኝ የተግባር ስራ ነው፡፡ በመሆኑም በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ የተማሩትን እውቀት ደጋግሞ በመለማመድ ወደ ተግባር በመለወጥ የሙዚቃ ክህሎት በቀላሉ እንዲኖረን እነዲሁም እንድናዳብር የሚያግዝና የሚያስችል የትምህርት ክፍል ነው፡፡

## 2.1 የድምፅና የእረፍት ምልክቶች

**የትምህርቱ ዝርዝር ዓላማ፡-**

ከዚህ ትምህርት በኂላ የሚጠበቁ ዝርዝር ውጤቶች፡-

- ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ የድምፅናየእረፍት ኖታ ምልክቶችን ትለያላችሁ
- ከሙሉ ኖታ እስ ከሩብ ኖታ ከነ እረፍት ኖታቸው በቀላል የምት መሳሪያዎች ተጫውታችሁ ታሳያላችሁ፡፡

ሙዚቃ ከሚከወንባቸው ኖታ ውስጥ ሙሉ ኖታ፣ ግማሽ ኖታ እንዲሁም ሩብ ኖታ ከአቻ የእረፍት ምልክቶች ጋር ይገኙበታል፡፡ እነዚህም ኖታዎች የራሳቸው የሆነ የጊዜ ቆይታና የአፃፃፍ ስነ ዘዴ አሏቸው፡፡

- የምልክቶቹም ታሪካዊ አመጣጥ በጊዜ ሂደት እየዳበረና እየተሻሻለ በመምጣት አሁን በዚህ ወቅት የምንጠቀምበትን የሙዚቃ ኖታ አጻጻፍ ስልት አለም አቀፋዊ ይዘትን በመያዝ ሙዚቃዊ ድምፆችን በወረቀት ላይ እንድንፅፍ አስችሏል፡፡

- በዚህ ክፍል ሙሉ ኖታ፣ ግማሽ ኖታ እንዲሁም ሩብ ኖታ ከነ እረፍት ምልክቶቻቸው በምት የሙዚቃ መሣሪያዎች በመታገዝ እንድንረዳ የሚያስችል ክፍል ነው፡፡
- በተጨማሪምቀላል የምት የሙዚቃ መሳሪያዎችን ለይተን እንድናውቃቸውም ያስችለናል፡፡

### 2.1.1 ሙሉ ኖታ

ሙሉ ኖታ ከሁሉም የኖታ አይነቶች ትልቅ የጊዜ ቆይታ ያለውና በሞላላ ክብ ቅርፅ የሚፃፍ የአራት ምት የጊዜ ዋጋ ያለው ነው፡፡ ይህ ምልክት አንድ ድምፅ ሳይቆራረጥ ለአራት ተከታታይ ምቶች የሚቆይ ነው፡፡



ምስል 1፡- የሙሉ ኖታ ምልክት

የኖታ (ምት) አቆጣጠር ሶስት ነገሮች አስፈላጊ ሲሆኑ እነሱም መነሻ መምታትንና ወደነበረበት ቦታ መመለስን ሲያጠቃልል የአንድ ምት ዋጋ ብለን እንጠራዋለን፡፡




ምስል 2፡- የአንድ ምት አቆጣጠር ዘዴ

የአንድ ምት አጨዋወትን በተለያየ ዘዴ መተግበር እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በእጃችን በማጨብጨብ፣ በእግራችን መሬትን በመምታት፣ በሁለት ጣቶቻችን (አውራ ጣትና መካከለኛ ጣትን) በማጋጨት፣ ሙሉ ሰውነትን ከግራ ወደቀኝ በማወዛወዝ፣ አንገትን ከላይ ወደታች ወይም ከቀኝ ወደግራ በማወዛወዝ ወዘተ… የአንድ ምትን ዋጋ በቀላሉ መተግበር እንችላለን፡፡

ሙሉ ኖታን በቀላሉ ለመረዳት በእጅ መዳፋችን አንድ ጊዜ ብቻ በማጨብጨብ እንዲሁም በእግራችን ደግሞ አራት ጊዜ መሬትን በመምታት (በመቁጠር) የምናገኘውን የጊዜ ቆይታን የሚወክል ነው፡፡



ምስል 3፡- አንድ ጊዜ የእጅ ጭብጨባ




ምስል 4፡- በእግር 4 ጊዜ በመምታት የሙሉ ኖታ (ምት) አቆጣጠር ዘዴ

የሙዚቃ አፃፃፍ ስልት (ኖታ) የሚያመለክቱት አንድ ኖታ የሚኖረውን የጊዜ ቆይታ ብቻ ሳይሆን ራሱን የቻለ የድምፆች መቅጠንና መወፈርን ይወክላል፡፡ ሙዚቃ በጆሮ የሚደመጥ ጥበብ በመሆኑ በድምፆችና በጊዜ ቆይታ ላይ ያተኩራል፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱ ኖታ የራሱ የሆነ ድምፅ ውክልና ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ በዚህ ርእስ ስር ድምፆች ላይ ሳይሆን የጊዜ ቆይታ ላይ ብቻ በማተኮር ግንዛቤ እንወስዳለን፡፡

ሙሉ ኖታ አራት ምት በአንድ ትንፋሽ ሳይቋረጥ መጫወት ነው፡፡ ይህም አንድን ድምፅ ለረጅም የጊዜ ቆይታ ያለምንም ማቆም እንድንጫወት ያስችለናል፡፡

**መልመጃ 1**

1. የሚከተሉትን የሙሉ ኖታ ምልክቶች ታ ሆሄን በመጠቀምና በመደጋገም ተለማመዱ፡፡




## 2.1.2 ሙሉ የእረፍት ኖታ

ሙሉ የእረፍት ኖታ ማለት ልክ እንደ ሙሉ ኖታ ሁሉ አራት ተከታታይ ምቶችን ሲወክል ምንም አይነት ድምፅ ሳይኖር በዝምታ የመቆየት ዘዴ ነው፡፡ ሙዚቃ ድምፅ በማውጣትና በዝምታ  በሁለቱም ጥምረት አማካኝነት የሚከወን ጥበብ ነው፡፡



ምስል 5፡- የሙሉ ኖታ የእረፍት ምልክት

ሙሉ ኖታ ከሙሉ እረፍት ኖታ  ምልክት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የጊዜ ቆይታ (ዋጋ) አላቸው፡፡




ምስል 6፡- የሙሉ ኖታና የሙሉ ኖታ እረፍት አቻ ምልክት

መልመጃ 2

የሚከተሉትን የሙሉ ኖታ ከነሙሉ እረፍት ምልክት እንደተፃፈው በመደጋገም ተለማመዱ፡፡ ድምፅ በሚኖረው ቦታ ታ ፊደልን በመጠቀምና የዝምታ ጊዜውን ምንም አይነት ድምፅ ባለማውጣት ተግብሩ፡፡




### 2.1.3 ግማሽ ኖታ

ግማሽ ኖታ ማለት የሙሉ ኖታ ግማሽ የጊዜ ቆይታ ያለውና በሞላላ ክብ ቅርፅ ላይ በቀኝ በኩል ወደላይ ሲሆን በግራ በኩል ደግሞ ወደታች የሚገናኝ መስመር ያለው ነው፡፡ ይህ ምልክት አንድ ድምፅ ሳይቆራረጥ ለሁለት ተከታታይ ምቶች የሚቆይ ነው፡፡




ምስል 7፡- ግማሽ ኖታ

ግማሽ ኖታ (ምት) የሙሉ ኖታን ለሁለት እኩል ማካፈል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሁለት ግማሽ ኖታዎች አንድ ሙሉ ኖታ ይሰጣሉ፡፡

ግማሽ ኖታን ለመጫወት በእጃችን አንድ ጊዜ ብቻ በማጨብጨብ በእግራችን ደግሞ ሁለት ጊዜ መሬቱን በመምታት መለማመድ እንችላለን፡፡



ምስል 8፡- አንድ ጊዜ የእጅ ጭብጨባ




ምስል 9፡- የግማሽ ኖታ ወይም 2 ምት የእግር አቆጣጠር

ግማሽ ኖታ ራስና ቀጥታ መስመር አለው፡፡ ራስ የሚባለው ሞላላ ክቡ ሲሆን ቀጥታ መስመር የሚባለው ደግሞ ከሞላላ ክቡ ጋር ወደላይ ወይም ወደታች የሚገናኘው መስመር ነው፡፡




ምስል 10፡- የግማሽ ኖታ ራስና ቀጥታ መስመር

ግማሽ ኖታ በሙዚቃ መፃፍያ ሰሌዳ ላይ የኖታውን ራስ ወደላይ ወይም ወደታች በማድረግ ሊፃፍ ይችላል፡፡

**መልመጃ 3**

1. የሚከተሉትን ግማሽ ኖታ ምልክትን በመመልከት ደጋግማችሁ ተለማመዱ፡፡




## 2.1.4 ግማሽ ኖታ እረፍት ጊዜ

የግማሽ እረፍት ምልክት ማለት ልክ እንደ ግማሽ ኖታ ሁሉ ሁለት ተከታታይ ምቶችን ሲወክል ምንም አይነት ድምፅ ሳይኖር በዝምታ ሁለቱንም የምት ቆይታ የመተግበር ዘዴ ነው፡፡



ምስል 11፡- ግማሽ እረፍት ኖታ ምልክት

**መልመጃ 4፡**

1. የሚከተሉትን ባለ ግማሽ ምት ኖታና አቻ የእረፍት ጊዜአቶችን ተለማመዱ፡፡ ኖታውን ለማንበብ <<ታ>>ፊደልን ተጠቀሙ፡፡ የእረፍት ምልክቶቹን በዝምታ አሳልፉ፡፡



### 2.1.5 ሩብ ኖታ

ሩብ ኖታ ማለት የሙሉ ኖታ ሩብ ወይም አንድ አራተኛ ማለት ሲሆን የግማሽ ኖታ ደግሞ ግማሹን የጊዜ ቆይታ የሚይዝ የሙዚቃ አፃፃፍ ስነ-ዘዴ ነው፡፡ ሩብ ኖታ እያንዳንዱን ምት በመቁጠር የሚገኝ ነው፡፡ ምልክቱም እንደግማሽ ኖታ የተቀለመ ሞላላ ክብ ራስና ቀጥታ መስመር ከኋላ ወደላይ ወይም ከፊት ወደታች የተሰመረበት ነው፡፡




ምስል 12፡- ሩብ ኖታ

አንድ ሩብ ኖታ ለመጫወት እጃችንን ከላይ ወደታች አንድ ጊዜ በመምታት እጃችን ወደ ነበረበት እስከሚመለስ ያለው የጊዜ ቆይታ ወይም በእግራችን ለመጫወት እግራችንን ከላይ ወደ ታች በመምታት እግራችን ወደ ነበረበት እስኪመለስ ያለው የጊዜ ቆይታ ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም ግራ ቀኝ ግራ ቀኝ በማለት መቁጠርም እንችላለን፡፡



ምስል 13፡- የሩብ ኖታ በእጅና በእግር የመጫወት ዘዴ

**መልመጃ 5**

1. ከተጻፈው የግጥም ፊደላት ጋር በኖታው የግዜ ቆይታ ውስጥ ተለማመዱ።




## 2.1.6 የሩብ ኖታ የእረፍት ምልክት

የሩብ ኖታ የእረፍት ምልክት ማለት አንድ ምት ብቻ ሲወክል በዚህም የምት ቆይታ ውስጥ ምንም አይነት ድምፅ ሳይኖር በዝምታ የመቆየት ዘዴ ነው።



ምስል 14፡- የሩብ ኖታ የእረፍት ምልክት

ይህም የዝምታ ምልክት ከሩብ ኖታ ምልክት ጋር እኩል ዋጋና የጊዜ ቆይታ አለው።



ምስል 15፡- የሩብ ኖታና አቻ የእረፍት ምልክት

ይህም የሩብ ኖታ የእረፍት ምልክት የሙሉ እረፍት ምልክትን አንድ አራተኛን ይወክላል፡፡ ይህም ማለት አራት ሩብ የእረፍት ምልክቶች አንድ ሙሉ የእረፍት ምልክት ኖታን ይሰጡናል ማለት ነው፡፡

መልመጃ 6

1. የሚከተሉትን የሩብ ኖታና የአቻ የእረፍት ኖታ ምልክቶችን ደጋግማችሁ አንብቡ፡፡ ኖታውን ለማንበብ <<ታ>> ፊደልን ተጠቀሙ፡ ፡ እጅ፣ እግር እንዲሁም ድምፅን በመጠቀም ተለማመዱ፡፡



2. የሚከተሉትን የሙሉ፣ የግማሽ፣ የሩብ ኖታዎችና የአቻ የእረፍት ምልክቶችን ደጋግማችሁ አንብቡ፡፡ ኖታውን ለማንበብ << ታ > > ፊደልን እንዲሁም የእረፍት ምልክቶቹን በዝምታ የምቱን የጊዜ ቆይታ ዋጋ በመቁጠር በመደጋገም ተለማመዱ፡፡



## 2.1.7 የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች

የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚባሉት በዱላ (ከበሮ መጫወቻ እንጨት) በመምታትና እርስ በእርስ በመጋጨት ድምፅ የሚፈጥሩ የሙዚቃ መሳሪያዎች ናቸው:: በሃገራችንም በርካታ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ይገኛሉ:: ከነዚህም ውስጥ ከበሮ፣ አታሞ፣ ፅናፅል፣ መቋሚያ፣ ድቤ፣ ከራቤ፣ ነጋሪት.....ወዘተ ይገኙበታል::

በእነዚህም ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ኖታዎችን መለማመድ ይቻላል::




ምስል 16:- ከባህላዊ የኢትዮጵያ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች በጥቂቱ



ምስል 17፡- የከበሮ መምቻ

**መልመጃ 7**

1.የሚከተለትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ወይም ስህተት ከሆነ ድግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

ሀ. ሩብ ኖታ አንድ ምት አለው፡፡

ለ. ሙሉ ኖታ ማለት ባለ ሁለት ምት ኖታ ነው፡፡

ሐ. የእረፍት ምልክት ድምፅ እናወጣለን፡፡

መ. ሩብ ኖታና ሩብ እረፍት እኩል ዋጋ አላቸው፡፡

ሠ. ግማሽ ኖታ ባለ ሁለት ምት ኖታ ነው፡፡

1. የሚከተሉትን ኖታዎች በእጆቻችሁ በከበሮ መጫወቻ (በከበሮ ዱላ) አማካኝነት ባህላዊ የምት የሙዚቃ መሳሪያዎች ላይ ተለማመዱ፡፡



## 2.2 የዳንስ ተግባራዊ ልምምድ

ዳንስ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ውስጣዊ ስሜትን፥ ፍቅርን፥ ንዴትን፥ ቅናትን፥ ጀግንነትን፥ ሀዘንንና የአካባቢ ውበትን በማድነቅ ከቃላትና ከቁሳቁስ ቀድሞ የነበረ በጠቅላላ አካላት አማካኝነት የሚገለፅ የእንቅስቃሴ ቋንቋ ነው፡፡

ዳንስ በእጅ እና የአንገት በላይ እንቅስቃሴዎች ባህርይ በሶስት ዓይነት ሁኔታዎች ይከፈላል።

1. ድርጊታዊ 2. ገላጭ 3. ድርጊትና ገላጭ በማለት ይከፈላሉ።

### 2.2.1 ድርጊታዊ የአንገት በላይ እንቅስቃሴዎች የሚባሉት

ለምሳሌ፦ የብርጭቆ ውሃ መጠጣት እንቅስቃሴ

- ወደ ክፍል ወይም ወደ ቤት ለመግባት የሚደረግ እንቅስቃሴ።



ስዕል 1

1. ገላጭ የእጅ እና የአንገት በላይ እንቅስቃሴዎች

- ለምሳሌ የብርጭቆ ይዘት ከአሸዋ የተሰራና አንፀባራቂ ብርሃን በውስጡ የሚያሳልፍ በመሆኑ።
- በብርጭቆ ጣፋጭ ነገር ስንጠጣ በውስጡ ያለው ፈሳሽ ነገር የሚሰጠው የጣፋጭነት ስሜቱ ሁኔታዎች ሂደት ነው።



ስዕል ፦2

3. ድርጊት ገላጭ የእጅ እና የአንገት በላይ እንቅስቃሴዎች ከላይ በተራቁጥር አንድ እና ሁለት የተጠቀሱት ተግባራት አንድ ላይ አጣምሮ የሚይዝ ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ፦ አንድን ሰው ጠጋ ይል ዘንድ የማዘዝ ሁኔታዎች ሂደት ገላጭ ሲሆኑ እንዲሁም ድርጊታዊም ናቸው፡፡

ጭንቅላትን ወደላይ፥ ወደታች ወደጎን ማወዛወዝ የእሺታን ወይም የእምቢታን ሁኔታ የመግለፅ ፡ የአመልካች ጣት የመጠቆም ወይም የአመልካች ጣትን ወደ አንድ ሰው የማወዛወዝ እንደማስፈራራት ወይም የማስጠንቀቅ ስሜትን ሁኔታ የመግለፅ በውስጥ የእጅ መዳፍ ወደ ግለሰብ መጠቆም ወይም ፊትን ከግለሰቡ ማዞር ሁኔታ የተቃውሞን ስሜት የመግለፅ፤ የእጅ ወደ ላይ ወደታች ፤ ወደጎን በመዘርጋት አቅጣጫን የመጠቆም ሁኔታዎች እና መሰል እንቅስቃሴዎች ትርጉም በማንኛውም ባህል ዘንድ የሚታወቁና ተቀባይነት ካላቸው እንቅስቃሴዎች መካከል ይገኛሉ፡፡





ስዕል፦ 3

- አንድ ሰው በቁጣ እጅን በሌላው ላይ የማወዛወዝ ወይም የማንቀጥቀጥ ሁኔታዎች ምናልባትም እንዳይጠጋው እንዲርቅ የማስጠንቀቅ ሊሆን ይችላል ይህ ገላጭም ድርጊትም ነው፡፡
- አንዳንድ የእጅ እና የአንገት በላይ እንቅስቃሴዎች አርማዎች ወይም ምልክቶች ለመሆን በመብቃታቸው የተነሳ በአጠቃላይ ማለት ይቻላል በማንኛውም ባህል ዘንድ የታወቁና ተቀባይነት ያገኙ ሆነው ይገኛሉ

3. ድርጊት ገላጭ የእጅ እና የአንገት በላይ እንቅስቃሴዎች ከላይ በተራ-ቁጥር አንድ እና ሁለት የተጠቀሱት ተግባራት አንድ ላይ አጣምሮ የሚይዝ ማለት ነው።

ለምሳሌ፦ አንድን ሰው ጠጋ ይል ዘንድ የማዘዝ ሁኔታዎች ሂደት ገላጭ ሲሆኑ እንዲሁም ድርጊታዊም ናቸው።

ጭንቅላትን ወደላይ፥ ወደታች ወደጎን ማወዛወዝ የአሺታን ወይም የእምቢታን ሁኔታ የመግለፅ ፡ የአመልካች ጣት የመጠቆም ወይም የአመልካች ጣትን ወደ አንድ ሰው የማወዛወዝ እንደማስፈራራት ወይም የማስጠንቀቅ ስሜትን ሁኔታ የመግለፅ በውስጥ የእጅ መዳፍ ወደ ግለሰብ መጠቆም ወይም ፊትን ከግለሰቡ ማዞር ሁኔታ የተቃውሞን ስሜት የመግለፅ፤ የእጅ ወደ ላይ ወደታች ፤ ወደጎን በመዘርጋት አቅጣጫን የመጠቆም ሁኔታዎች እና መሰል እንቅስቃሴዎች ትርጉም በማንኛውም ባህል ዘንድ የሚታወቁና ተቀባይነት ካላቸው እንቅስቃሴዎች መካከል ይገኛሉ።



ስዕል፦ 3

- አንድ ሰው በቁጣ እጅን በሌላው ላይ የማወዛወዝ ወይም የማንቀጥቀጥ ሁኔታዎች ምናልባትም እንዳይጠጋው እንዲርቅ የማስጠንቀቅ ሊሆን ይችላል ይህ ገላጭም ድርጊትም ነው።
- አንዳንድ የእጅ እና የአንገት በላይ እንቅስቃሴዎች አርማዎች ወይም ምልክቶች ለመሆን በመብቃታቸው የተነሳ በአጠቃላይ ማለት ይቻላል በማንኛውም ባህል ዘንድ የታወቁና ተቀባይነት ያገኙ ሆነው ይገኛሉ

## ስሜታዊ መገለጫዎች ስዕል 7






1- ተማሪዎች የተለያዩ አይነት እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ለመምህራችሁ አሳዩ::
2- የተለያዩ ስሜታዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ለመምህራችሁ አሳዩ::

### መልመጃ 1

1- ዳንስ ምን ማለት ነው?
2- እንቅስቃሴ በምን በምን ይገለፃል?

## 2.2.2 መልዕክቶች በድራማ፣ በቪዲዮና በፎቶግራፍ፤ የዳንስን እና የጨዋታ ጭብጦችን መለየት

ተማሪዎች በምዕራፍ አንድ ስለ ድራማ ምንነት ተገንዝባችኃል። ድራማ ለመዝናናት ፋይዳ ሲባል የሌሎችን ባሕርይ ሁናቴና ንግግር ለጊዜው ወርሶ ክዋኔን ከቋንቋ ጋር አገናኝቶ መጫወት ማለት እንደሆነ። በዚህ ክፍል ሁለት ፈጠራዊ ግንዛቤና ተግባራዊ ልምምድ አለ

ድራማ ክዋኔ፡ አከናወን ወይም ማስመሰል፤ መልዕክቶች በፎቶ እና በቪድዮ እንድታውቁ ይጠበቃል።

የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፡-

ይህንን ትምህርት ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ስለ ድራማ ምንነት ትረዳላችሁ።
- ማስመሰል ወይም አከታተብ ትገነዘባላችሁ
- ተረቶችን በድራማ መልክ እየተረኩ ታቀርባላችሁ።
- የቪድዮ የፎቶ መልዕክቶች ትመለከታላችሁ።
- የዳንስ አይነቶችን ትረዳላችሁ።

ተውኔት ከሰው ልጆች እውነተኛ ድርጊት የሚከተብ የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ነው። ስለዚህ በትምህርት ቤታችሁ፥ በየቤታችሁ እና የተለያዩ ቦታዎች መስራት ትችላላችሁ ማለት ነው። ስለዚህ የልጆችን ዕቃ ዕቃ ጨዋታዎች፣ባህላዊ ስርዓቶች፣ ሃይማኖታዊ ክንዋኔዎችን፣ የመሳሰሉትን ሁሉ "ነገረተውኔት" የተውኔት ወይም ድራማ ገጽታ እንዳላቸው ልትገነዘቡ ይገባል።

ስለዚህ ተውኔት በሁለት መንገዶች ይከወናል የመጀመሪያው ህዝባዊ ወይም በማህበረሰቡ በወል የሚከወኑ፣ያልተወሳሰቡ ወይም መደበኛ ቦታ የሌላቸው ሲሆኑ፣ ሁለተኛው ደግሞ በቤተ ተውኔት የሚቀርቡት ናቸው፡፡

ይህም ተውኔት ተፅፎ፣ በመራሄ ተውኔት አማካኝነት ተዋንያን ተመልምለው፣ ቃለ-ተውኔት ተጠንቶ፣ ድምፅ፣ አልባሳት፣ መብራት፣ መዋቢያ፣ ተሟልቷል ለህዝብ የሚቀርብ የተወሳሰበ ባህሪይ እና ሴራ ያለው ነው፡፡

### 2.2.3 ማስመሰል፤ አከታተብ (imitation)

አከታተብ ወይም ቅፀላ የሚለው ቃል ትርጉሙ አስመስሎ መፃፍ፥ አስመስሎ መራመድ፥ አስመስሎ መናገር፥ አስመስሎ መልበስ፥ በአጠቃላይ አሰመስሎ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ሰዎች በተፈጥሮአቸው ያዩትን ነገር ሁሉ አስመስለው በመክተብ ወይም በመቅዳት የሚስተካከላቸው እንደሌለ አርስጣጣሊስ ይናገራል፡፡ ማንም ሰው ገና ህፃን እንዳለ መብላት፣መጠጣት፣መሄድ፣መናገር ወዘተ.. የሚማረው ሌሎች ሰዎችን በተለይም ወላጅ ዘመዶችን እየከተበ ወይም እየቀፀለ ነው፡፡ በተውኔት አለም አከታተብ ወይም ቅፀላ የሚለው ቃል የተለመደ ነው፡፡ ከዘህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጨዋታዎች በማስመሰል ተጫወቱ፡፡

ጨዋታ፦ ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት ሁለት ጨዋታዎች የማስመሰልን ችሎታ እንዲዳብር የፈጠራ አቅማችሁ እንዲጎለብት፤ እንዲሁም ለማዝናናት እና ለማፍታታት ይጠቅማል፡፡

### 2.2.4 ምን አየህ?

በክፍል ውስጥ ሆነ ከክፍል ውጭ በክብ ወይም በረድፍ በመቀመጥ ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ያለውን መምህራችሁንም ሆነ የክፍል ጓደኛችሁን የፈለገውን ዐይነት ልዩ ልዩ ድርጊቶች በምልክት ወይም እንቅስቃሴ እየሰራ ያሳያችኃል፡፡ ምን እንደሰራ ያያችሁትን ነገር ልክ እሱ እንዳደረገው በማድረግ መድገም፡፡

### 2.2.5 ጓደኛ መፈለግ፤

ክብ መስመር አዘጋጅቶ ልጆቹ ከመስመሩ ውጭ በክብ ዙሪያ መቆም ትእዛዝ ሲሰሙ በአንድ አቅጣጫ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ በዝግታ ሩጫ መንቀሳቀስ፤ መምህሩ ለሁለት ለሁለት ወይም ሶስት ሶስት ተያያዙ ሲል ሁሉም ጓደኛውን ፈልጎ መያዝ ወይም መያያዝ:: ጓደኛ ያላገኘ ልጅ ከጨዋታው ውጭ ይሆናል:: በዚህ ሂደት መጨረሻ የቀረው ልጅ አሸናፊ ይሆናል::

ስዕል 1



ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡት የክቡር ከበደ ሚካኤል ተረት በማንበብ እና በቃላችሁ በመያዝ ለመምህራችሁ አቅርቡ:: ቀጥሎ የቀረቡት የክቡር ከበደ ሚካኤል ተረቶች ተማሪዎች ስለ እንሰሳት ሰነ-ባህሪ እና ስለ ፍቅር አስፈላጊነት ግንዛቤ ያስጨብጣል::

### 2.2.6 ጨዋታ የሚወድ ልጅ

ብራ የሆነ አንድ የበጋ ቀን ነበርና አንድ ትንሽ ልጅ በናቱ ፈቃድ ወደ ተማሪ ቤት ተልኮ ሄደ:: እርስዋ ግን ጨዋታ እንደሚወድ አላወቀችምና እኅቱ ከርሱ ጋር እንድትሄድ አዘዘች::

ቀኑም ሙቀት ነበርና ልጁ አንስቶ እኅቱን ወደ ተማሪ ቤት ከመሄድ ይልቅ ብንጫወት እጅግ መልካም ነበር አላት:: እርስዋ ግን እንኳን አይደለም አሁን ለጨዋታ ጊዜ የለኝምና አንተን ወደ ተማሪ ቤት ካደረስኩህ በኋላ ጥጥ ሐርና መርፌ ሌላም ብዙ ነገር ለናታችን እንድገዛላት ወደ ከተማ እሻገራለሁ:: ምግብ ለማግኘትም ገንዘብ እንድናገኝ ግድ ሥራዬን እሠራለሁ አለችው::

ከዚህ በኋላ ይኸው ልጅ አንዲት ንብ ከአበባ ወደ አበባ ስትበር አየና ንብ ለመሆን እወዳለሁ እርሷ ስራ የላትም እኔም ስራ የለኝም አለ፡፡ እኅቱ ግን ዋይ ብላ ንቢቱ እኮ ሰነፍ አትምሰልህ ማር ታገኛለች፤ አበባም በሌለ ጊዜ ለክረምት እንዲሆናት ትሰበስባለች፡፡ ንቢቱ አበባውን ይዛ ወደ ቀፎዋ ትመለሳለች አለችው፡፡ ወዲያውም አንድ ወፍ ስትዘፍን ሰማና ይህች ወፍ በርግጥ አሁን ሥራ የላትም ቀኑንም ሁሉ መልካም ዘፈን ትዘፍናለችና በዛፉ ስር ተቀምጠን እርስዋን ብንሰማ እወዳለሁ አለ፡፡ እኅቱም መልሳ ወፊቱ ትበራለች ገለባውንም ሰብስባ አሁን ወደ ጎጆዋ ትወስዳለች፡፡ በላባና በገለባ በቅርጫፍም ጎጆዋን ትሰራለች፤ ስለዚህ ለመስነፍ ጊዜ የላትም

አለች፡፡

ሄደውም ሳይጨርሱ በመንገድ አጠገብ  አንድ ውሻ ባዩ ጊዜ ይህ ውሻ የሚያደርገው አንዳች ነገር ያለ አይመስለኝም፤ ስለዚህ ከርሱ ጋር ለመጫወት አይፈቀድልኝምን እያለ ሲነጋገር ወዲያው አንድ ሰው አፏጨ፡፡ ውሻውም ፈጥኖ ተነሳና በጎቹን ወደ ገበያ ሊወስድ የሚነዳውን ሰውዬ ለመርዳት ሄደ፡፡

እንደ ገናም ልጁ እልፍ ሲል አንድ ፈረስ በመስክ ሲግጥ አየና ይህ ፈረስ የሚያደርገው የለውምና ስለዚህ ሄጄ ከርሱ ጋር እጫወታለሁ አለ፡፡ ነገር ግን ጥቂት ወደፊት እንደ ተራመደ ሰውዬው ልባብ ይዞ ቀረበና ፈረሱን ለበበው፡፡

እንዲህም እንዳደረገ ልጁን ጠራና ልጄ ሆይ ፈረሴ ያርሳል፤ ይተልማልም፤ ገንዘብም እንዳገኝ ረገማ ገብስ ስንዴ ፈጭቶ ለመሸጥ ግድ ያስፈልገናል፤ ብሎ መንገዱን ቀጠለ፡፡

ከዚህ በኋላ ይህ ልጅ ንብ ወፍና እንስሳ ሥራ እንዳላቸው ባየ ጊዜ እኅቱን እንዲህ አላት፤ እኅቴ ሆይ እንዲህስ ከሆነ እኔም ወደ ተማሪ ቤት ሄጄ ትምህርቴን አጠናለሁ፤ ወደ ቤቴም ስመለስ ሳልተኛ ረጅም ጊዜ ከባልንጀሮቼ ጋር ለመጫወት እናቴ ትፈቅድልኛለች፡፡

እንዲህም እያለ ወደ ተማሪ ቤቱ ሮጠ፡፡ እኅቱም ከርሱ ስለተለየች መልዕክትን ለማድረስ ደስ እያላት ሄደች፡፡ ሰንፍናን የሚወልድ ኀዘን ይሆንበታል፡፡

**መልመጃ አንድ**

1- ከዚህ ታሪክ ምን ተረዳችሁ?
2- ጨዋታ የሚወድ ልጅ እንደምን ያለ ነው?
3- ጨዋታ የሚወደው ልጅ ከማን ከማን ድርጊት ትምህርት ቤት መሄድ እንዳለበት ተረዳ?

ቀጥሎ የቀረቡት የክቡር ከበደ ሚካኤል ሁለት ተረቶች ተማሪዎች ስለ እንሰሳት ባህሪ እና ስለ ፍቅር አስፈላጊነት ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡

## 2.2.7 አንበሳ

አንበሳ የአራዊት ንጉሥ ይባላል፡፡ የሚያስፈራና ግርማ ሞገስ ያለው ኀይለኛም አውሬ ነው፡፡ ብዙ አንበሶች የሚገኙበት ስፍራ በአፍሪቃ ውስጥ ባለው በሰፊው ሜዳና በልዩ ልዩ ተራሮች ላይ ራቅ ብለው ነው፡፡ በእዚያም

ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን እንደ አፍሪቃ አንበሶች ብርታትና ትልቅነት የላቸውም፡፡

አንዳንድ ጊዜም ቀን ለቀን ሲሄዱ ይታያሉ የሆነ ሆኖ አንበሳ ፀሐይ ሲጠልቅ ዋሻውን ትቶ ወደ አደን ይሄዳል፤ ሲራመድም ቀስ ብሎ እያደባ ነው፡፡ እንዲ ዱካው አይሰማም ፍለጋውም እንዳይታይ በጭራው እያጠፋው ይሄዳል ይበላል፡፡ ጸጥ ባለ ጊዜም የሚያስፈራ ድምጹን ያሰማል፤ በሌሊትም እንደ ነጎድጓድ ያስደነግጣል፡፡ ወደ መንደርም በቀረበ ጊዜ ውሾች ጩኸታቸውን ያሰማሉ በቤትም ውስጥ ያሉ እንስሳት ሁሉ ድምጹን ያውቃሉና በፍርሃት ይናወጣሉ ይርበደበዳሉ፡፡ ሰዎችም እርሱን ለማብረር ሲሻቸው ችቦ አብርተው ያወዛውዛሉ፡፡ አንበሳው ግን ከቁም ነገር አይቆጥረውም፡፡ ከብት ወደሚኖርበት ስፍራ ሄዶ እንስሶችን ይሰብራልና በዚህ ምክንያት የሰሜን አፍሪቃ ሰዎች ከመንጎቻቸው ብዙ ያጣሉ፡፡

ስለሆነም አንበሳ አንዳንድ ጊዜ ሳይመሽ ቀደም ብሎ ዋሻውን ይለቃል በተራበ ጊዜም ቀን ለቀን ሜዳ ለሜዳ ሲዞር ይገኛል፡ በዚያም የሜዳ አህዮችና አጋዘኖች መንጋ ሆነው ወዲያና ወዲህ ሲሉ ይገኛሉ በሩቅም ሳለ ያንበሳው ጠረን ይሰማቸዋል፡፡

ድምጹንም በሰሙ ጊዜ በበረሃው እንደ ነፋስ ይበራሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜም በድንጋጤ ተንበርክከው አንበሳው ወደ ተሸሸገበት ይደርሳሉ፤ ከዚህ በኋላ ያደፍጥና ዐይኑን አፍጥጦ ያያቸዋል፡፡ ወዲያውም ባንድ ዝላይ ድል ይነሳቸዋል፡፡

አንበሳ ረዥም ጎፈር ያለው ዳለቻ መሳይ ነው፡፡ እንስቲቱ አንበሳ ከተባቱ አንበሳ አነስተኛ ናትና ጎፈር የላትም መኖሪያዋንም ድፍቅ በሆነ ዱር ወይም በደን ውስጥ ታደርጋለች በዚያም ከግልገሎቿ ጋር ትኖራለች አንበሳይቱ በዋሻዋ ሳለች ለሚደርስ አውሬ ወይም ሰው ወዬለት፡፡

## 2.2.8 ፍቅር

ፍቅር ፉክክርን፣ ትምክሕትን፣ ታሸንፋለች፡፡

አምስት ጣቶች እኔ አዝዛለሁ፤ እኔ አዝዛለሁ በማለት ተጣልተው ወደ ዳኛ ሄዱና እያንዳንዳቸው ቀጥሎ ያለውን ይነጋገሩ ጀመር፡፡ መጀመሪያ አውራ ጣት እንዲህ ብሎ ቃሉን አቀረበ፡፡ ከሁላችሁ የበለጥሁ ወፍራም ነኝ፡፡ በትግልም ከናንተ አንድም የሚያሸንፈኝ የለምና ለኔ እንድትታዘዙኝ ነው የሚገባችሁ አላቸው፡፡

ሌባ ጣትም ይህንን በሰማ ጊዜ እንዲህ ብሎ መለሰ አንተ ብትወፍር ይልቅ ካንተ የበለጥሁ ዐዋቂ እኔ ነኝ፡፡ ሰውዩውም በኔ አድርጎ የፈለገውን ይነጋገራል፤ ያመለክታልም ስለዚህ ሁላችሁም ለኔ እንድትታዘዙልኝ ይገባችኋል አላቸው መሐከለኛው ጣትም ይህንን ሰምቶ እንዲህ ብሎ መለሰ፡፡ አንተም ብትወፍር አንተም ብታውቅ ከሁላችሁ ይልቅ የበለጥሁ ረጅም እኔ ነኝና ለኔ ልትታዘዙልኝ ይገባችኋል አላቸው፡፡

የቀለበትም ጣት እንዲህ አላቸው፡፡ እናንተ እኔ ከበርቴው እያለው ምንድን ነው የምትባባሉት፡፡ ሰውም ሁሉ እኔን ነው የሚሸልመኝ፡፡ ስለዚህ ለኔ ለከበርቴው ልትታዘዙልኝ ነው የሚገባችሁ አላቸው፡፡

ትንሹም ጣት ፋንታውን ተነሳና እባካችሁ ወንድሞቼ ይህ ሁሉ ንግግራችሁ አላማረኝም፡፡ ይልቅ ብትቀበሉኝም ባትቀበሉኝም ትንሽ የምክር ቃል ልንገራችሁ አዳምጡኝ ብሎ ሰበሰባቸውና የምክሩን ቃል እንዲህ ብሎ ያከታትል ጀመር፡፡ ወንድሞቼ ሆይ ለምን በማይረባ ነገር ትጣላላችሁ እኔ አዝዛለሁ እኔ አዝዛሉ ብትባባሉ መቼም የሰውየው ታዛዦች ነንና ተስማምተን ስራችንን እንድንሰራ እኔ ትንሹ ወንድማችሁ አጥብቄ እለምናችኋለሁ ለዚሁ የሚስማማውን ጥቅስ ልጥቀስላችሁ ብሎ ቀጥሎ ያለውን ጠቀሰላቸው፡፡ አንድነትና መስማማት ኃይል ይሰጣል፡፡

**መልመጃ ሁለት**

1- ስለ አንበሳ ምን ተማራችሁ?
2- አንበሳን በምን ምሳሌ ልናደርገው ይገባል?
3- ስለ ፍቅር አስፈላጊነት ምን ተገነዘባችሁ?

### 2.2.9 የፊልም ጥበብ አጀማመር

ፊልም 1832 እ ኤ አ በቤልጂማዊ ሳይንቲስት ጆሴፍ እንቶኒ ለአለም ተዋውቋል፡፡ ተንቀሳቃሽ ምስል ከፎቶ ግራፍ ጥምረት የሚቀመር የእይታ ጥበብ እና ተከታታይነት ያለው ትረካ በውስጡ የያዘ ጥበብ ነው፡፡ በአለም ላይ የማይንቀሳቀሱ ስዕሎች በሰአሊያን መፈጠር የፎቶግራፍ ጥበብ እንዲታሰብና እንዲፈጠር አስችሎታል፡፡

የፊልም ጥበብ አጀማመር በኢትዮጵያ ስንመለከት የቴክኖሎጂ ትውውቅ መሰረትን በማድረግ ከመብራት፥ የስልክ፥ ትራንስፖርትና ሌሎች ኢንዱስትሪ አውታሮች ሲተዋወቁ ፊልም ጥበብም በአውሮፓ ከተዋወቀ በአጭር ጊዜ ውስጥ በአፄ ምኒልክ አማካኝነት በ1889 ዓ.ም የመጀመሪያው ፊልም ከነ ማጫዎቻ መሳሪያው ወደ ሀገር ውስጥ ሊገባ በቅቷል፡፡

በኢትዮጵያ የፊልም ታሪክ በ1912 ዓ.ም የተሰራው ዘጋቢ ፊልም ስለ ንግስት ነገስታት ዘውዲቱ የንግስና ስርዓት የሚያሳይ ሲሆን፤ 1956 ዓ`ም“ ሂሩት አባትዋ ማን ነው” የመጀመሪያዎቹ በሀገራችን የተሰሩ ናቸው::

## መልመጃ ሶስት

ከዘህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ

1- የፊልም ጥበብ ማለት ምን ማለት ነው?

2- ለፎቶግራፍ መፈጠር ምክንያቱ ምን ነበር?

## 2.4 ቀለል ያሉ ቅርጾች ውጫዊ አካል መሳል ፎርሞች ማቅለል

ተማሪዎች ይህንን ከተማሩ በኃላ፡-

- ቀለል ያሉ ቅርጾች ውጫዊ አካል መሳል ታውቃላችሁ
- ፎርሞችን ትረዳላችሁ
- መሰረታዊ ቀለማትን ትለያላችሁ
- በቀለማቱ ቀጥተኛ ህትመት ትቀባላችሁ

### 2.4.1. ቀለል ያሉ ቅርፆች ውጫዊ አካል መሳል

ተማሪዎች በዚህ ትምህርት ክፍል የቅርጾችን ውጫዊ አካል እንስላለን የቅርፆቹን ለመሳል መጀመሪያ የተሰጠንን ወይም ያሰብነውን ምስል ምን እንደሆነ መረዳት አለብን:: የተሰጡን ቅርጾች ጂኦሜትሪካዊ ወይንም ተፈጥሯዊ ሲሆኑ ይችላሉ::

ምሳሌ



### 2.4.2 ጂኦሜትሪያዊ ፎርሞች

በአብዛኛው የሰው ልጅ የሚገለገልባቸው አይነቶች ሲሆኑ ታስበው ተጠንተው የሚሰሩ ናቸው። የጂኦሜሪያዊ ፎርሞች ያላቸው

ምስል 1



በቤት ውስጥ የምንገለገልባቸው የጂኦሜትሪያዊ ፎርሞች ያላቸው ነገሮች ለምሳሌ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ ጀበና፣ መጽሐፍ ወዘተ

ምስል 2








ከምንመገባቸው ፍራፍሬዎች መሀል የጂኦሜትሪካዊ ፎርሞች ያላቸው ነገሮች ለምሳሌ ብርቱካን ፣ካሮት፣ ሀባብ ወዘተ

### 2.4.3 ፎርሞችን ማቅለም

ተማሪዎች ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኃላ የተለያዩ ፎርሞችን

እናቀልማለን፡፡ፎርሞችን ስንል የምናየው ነገር ዙሪያውን ማለት ነው በዕይታ ጥበብ ውስጥ መሰረታዊ ከሚባሉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡

ምስል 3






**መልመጃ 1**

1. ተማሪዎች የተሰጣችሁን ውጫዊ አካል በመሳል ቀቡ
2. ተማሪዎች በተሰጣችሁ ምስል ፎርሞች በደብተራችሁ ላይ ደጋግማችሁ በመሳል ቀቡ
3. የተማሪዎች የነገሮችን ው ጫዊ አካል መሳል ምን ማለት እንደሆነ መረዳታችሁን በስዕል ግለጹ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከከሆነ እውነት ወይም ስህተት ከሆነ ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።

1. የቅርጾችን ውጪአዊ አካል መሳል ማለት ያየነውን ነገር በእርሳስ ንድፍ መስራት ማለት ነው
2. በቤት ውስጥ የምንገለገልባቸው ነገሮች አብዛኛው የጂኦሜትሪካዊ ቅርጽ አላቸው

## 2.4.4 መሰረታዊ ቀለማት ቀጥተኛ ህትመት

ተማሪዎች ይሄንን ትምህርት ከተማራችሁ በኃላ

- መሰረታዊ ቀለማትን ታውቃላችሁ
- ባወቃችዋቸው ቀለሞች ህትመት ትሰራላችሁ

## 2.4.5 መሰረታዊ ቀለማት

መሰረታዊ ቀለማት ምንድን ናቸው ?

መሰረታዊ ቀለማት ስንል የትኛውም ቀለም ተደባልቆ ሊፈጥራቸው የማይችላቸው እራሳቸውን ችለው የቆሙ ቀለማት ናቸው። እነርሱም ቢጫ፣ ቀይ፣ ሰማያዊ ናቸው በእነዚህ ሶስት ቀለማት ግን ሌሎች ቀለማትን መፍጠር እንችላለን።

ምስል

መሠረታዊ ቀለማት



ቀይ ቢጫ ሰማያዊ

## 2.5.1 መሰረታዊ ቀለማትን ተጠቅመን ቀጥተኛ ህትመት መስራት

## 2.5.2 ማተም

ማተም ማለት የተለያዩ ምስሎችን እየደጋገምን እንድንሰራ የሚጠቅመን የዕይታ ጥበብ አይነት ነው። ከላይ የተማርናቸው ቀለማት ተጠቅመን በቅጠል ማተም

አሰራር

- ቅጠል፣ የስዕል ብሩሽ፣ መሰረታዊ ቀለማት፣ ትንሽ ውሃ፣ ቀለም መበጥበጫ ሰሀን፣
- ቅጠሉ በጀርባው በመቀባት ወረቀቱ ላይ መለጠፍ
- ቅጠሉ ላይ ከበድ ያለ ነገር ለትንሽ ጊዜ መጫን
- ቅጠሉን ማንሳት
- አካባቢን ማጽዳት

**ምሳሌ**



## 2.5.3 በድንች የሚሠራ ህትመት

አሰራር

- ድንች
- ድንቹን ለሁለት መክፈል "እርጥቦቹን በጨርቅ ማጽዳት"
- ድንቹ ላይ "የፈለግናቸውን ቀላል ምስሎች መቅረጽ" የቤተሰብና /የመምህር እርዳታ ያስፈልጋል
- ድንቹ ላይ የቀረጽነውን ምስል ቀለም መቀባት
- በወረቀት ላይ ማተም

ምሳሌ





ማጠቃለያ

ከዚህ በፊት ከሙሉ ኖታ እስከ ሩብ ኖታ ከነ አቻ እረፍት ኖታ (ምልክታቸው) ከጊዜ ቆታቸው ጋር ማንበብና በቀላል የምት መሳሪያዎች ተለማምዳችኋል፡፡ ይህም እወቀት እንዳይረሳ ደጋግሞ መለማመድ ይገባል፡፡

የማተም የዕይታ ጥበብ ነገሮችን ደጋግመን እንድንሠራቸው ይረዳናል ከላይ ከሰራናቸው የማተም ሂደቶች በተጨማሪ በእጆቻችን በእግሮቻችን ላይ በመቀባት የተለያዩ ምስሎች መስራች እንችላለን

## የማጠቃለያ ምዘና

1.የሚከተሉትን ኖታ ከአቻ እረፍት ምልክታቸው ጋር አዛምዱ




2. ስሜት በስንት አይነት አካላዊ እንቅስቃሴ ይገለፃል? እነሱን ጥቀሱ?

3.የፊልም ጥበብ በኢትዮጵያ መቼ ተዋወቀ?

4.በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራው ተንቀሳቃሽ ምስል ምን ነበር?

2.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆነ እውነት ወይም ስህተት ከሆነ ደግሞ ሐሰት በማለት መልሱ፡፡

1.የድንች ሕትመት የዕይታ ጥበብን ከሰራን በኃላ የሰራንበትን መገልገያዎች

እዛው ጥለን መተው አለብን፡፡

2.በድንች የሚሠራ ህትመት ላይ ድንቹን ለመቁረጥ የቤተሰብ እና የአስተማሪ

እርዳታ ያስፈልጋናል፡፡

3. የማተም ጥበብ ነገሮች ደጋግመን እንድንሰራ ያደርጋል፡፡

4. መሰረታዊ ቀለማት የምንላቸው ነጭና ጥቁር ናቸው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## ታሪካዊና ባህላዊ አውድ/አግባብ/

### መግቢያ

ባህል ማለት የአንድ ህዝብ ወይም ህብረተሰብ ረዘም ላለ ጊዜ ይዞ ያቆየው የአኗኗር ስልት፣ የአመጋገብ ሁኔታ፣ የሃይማኖት ስርአቶች፣ አለባበስ፣ ቋንቋ፣ ሙዚቃ፣ ስዕል፣ መገልገያ ቁሳቁሶች ወዘተ…ከትውልድ ወደ ትውልድ የማሸጋገር ሁኔታ ነው::

ባህል ሰዎች በጊዜ ሂደት አብሮ በመኖር የሚያዳብሩት፣ የሚጋሩት፣ የሚማሩትና የሚያስተምሩት እንዲሁም ከትውልድ ትውልድ የሚያሸጋግሩት የኑሮ ሂደት ነው:: የአንድ ሀገር ህዝብ ተመሳሳይ የሆነ ባህል ሊኖረውም ላይኖረውም ይችላል:: በመሆኑም ተከባብሮና ተዋዶ መኖር ተገቢ ነው::

ብዙ ዓይነትባህሎች በአንድ ሀገር ውስጥ በሕብረት ሲኖሩ <<ብዝሀ ባህል>>አለ ማለት እንችላለን:: ብዝሀ ባህል ባለበት እነዚያ ባህሎች ልዩ ልዩ አይነት የዕይታ ጥበባት በመባል ይታወቃሉ:: በዚህ ምዕራፍ ተማሪዎች ያለፈውንና የአሁን ብዝሀ ባህል ላይ ያተኮሩ የዕታ ጥበባትን እንቃኛለን::

## አጠቃላይ የትምህርት ውጤት፡

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ካጠናቀቁ በኂላ፡-

- ባህላቸውን ትረዳላችሁ፡፡
- ስለ ብዝኃ ባህል ላይ ያተኮረ ያለፈውንና የአሁኑን የክወናና ዕይታ ጥበባት ትረዳላችሁ፡፡
- ስለ አገራዊ ውዝዋዜ ታውቃላችሁ፡፡
- የታዋቂ ሰዎች ታሪኮችን ታነባላችሁ፡፡
- የቀለም፣የሙዚቃ፣የውዝዋዜና የድራማ ባህላዊ ገፅታን ትረዳላችሁ፡፡

ባህል በአንድ ሀገር ማህበረሰብ የኑሮ ሁኔታ የሚገለፅበት በመሆኑ በሙዚቃ ጥበብ የአኗኗር ዘይቤውን ይገልፅበታል፡፡ በመሆኑም በዚህ ክፍል በሃገራችን ያሉትን ባህሎች በሙዚቃ ለመግለፅ እንሞክራለን፡፡

## የትምህርቱ ዝርዝር አላማ

ተማሪዎች ይህን ትምህርት ከተማራችሁ በኂላ፦

- የቤተሰባዊ ሚናዎችን በመዘመር፣ በውዝዋዜ፣ በሚና ጨዋታ በማስመሰል ታሳያላችሁ፡፡
- የአካባቢውን ጥበብ በመዘመር ታቀርባላችሁ፡፡

## 3.1 በብዝሃ ባህል ላይ ያተኮረ ያለፈውና የአሁን የሙዚቃ ጥበብ

ብዝሃነት ማለት የተለያዩ ባህል፣ ቋንቋ፣ አመጋገብ፣ ኪነጥበብ፣ አለባበስ ወዘተ…በአንድ ሃገር ውስጥ በህብረት መገኘት ነው፡፡ እነዚህ ልዩነቶችን በእኩልነት በማየትና የሌሎችን አኗኗርና ባህል በማክበር በአንድነት መኖር ተገቢ ነው፡፡ በሃገራችን ቀደም ካሉት ጊዜአት ጀምረን ስንጠቀምባቸው የነበሩትንና አሁንም በጥቅም ላይ ያሉትን የዜማ አይነቶችን እናያለን፡፡ በኢትዮጵያ ከሰማኒያ በላይ ብሄር ብሄረሰቦች በአንድነት ሲኖሩ ከአርባ በላይ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡፡ እነዚህም ብሄር ብሄረሰቦች ባህላቸውን በሙዚቃ ይገልፃሉ፡፡

ሙዚቃ ለሰው ልጅ ለብዙ ጉዳዮች መግለጫነት ያገለግላል፡፡
ከነዚህም ውስጥ፡-

### 3.1.1 ለደስታ መግለጫነት የሚዜም ዜማ፡- ለሰርግ፣ ለልደት፣ ለተለያዩ

ግብዣዎች፣ ለምርቃት፣ ህዝባዊና መንግስታዊ በአላትን ለማድመቅ የሚዘፈኑ ሲሆን በውስጣቸው የደስታ መልእክቶችን የያዙ ናቸው፡፡

ምሳሌ 1፡- የልደት መዝሙር



<u>መልካም ልደት መዝሙር</u>

መልካም ልደት ላንተ

መልካም ልደት ላንቺ

መልካም ልደት

መልካም ልደት

መልካም ልደት ላንተ(ቺ)

**መልመጃ 1፡- የምታውቁትን የልደት መዝሙር ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ ዘምራችሁ ለየብቻችሁና በቡድን አሳዩ፡፡**

**ምሳሌ 2፡- የሰርግ ሙዚቃ**




**መልመጃ 2፡- በአካባቢያችሁ የምታውቁትን የሰርግ ዜማ ለመምህራችሁ ዘምራችሁ አሳዩ፡፡**

**3.1.2 የክብረ በአላት ዜማዎች፡-** ባህላዊ ለሆኑክብረ በአላት የሚዜሙ ዜማዎች ናቸው፡፡ ቡሄ፣ አበባየሆሽ፣ አሸንዳ፣ አሸንድዬ፣ ጨምበላላ…ወዘተ ይጠቀሳሉ፡፡




ምሳሌ 3፡- ቡሄ

<u>የቡሄ ግጥም</u>

መጣና ባመቱ እንዴት ሰነበቱ

መጣና መጣና ደጅ ልንጠና

ሆያ ሆዬ ሆ

ሆያሆዬ ሆ

እዛ ማዶ ሆ

ጭስ ይጨሳል ሆ

አጋፋሪ ሆ

ይደግሳል ሆ

ያችን ድግስ ሆ

ውጬ ውጬ ሆ

ከድንክ አልጋ ሆ

ተገልብጬ ሆ

ያቺ ድንክ አልጋ ሆ

አመለኛ ሆ

ያላንድ ሰው ሆ

አታስተኛ ሆ

ሆያ ሆዬ ነው የምንለው፡፡

አመት አውዳመት

ድገምና

አመት ድገምና

ያባብዬን ቤት

ድገምና አመት ድገምና

የማምዬን ቤት

ድገምና

አመት ድገምና

መልመጃ 3፡- ተማሪዎች ከላይ የተቀመጠውን የቡሄ ግጥም በዜማ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

ቡሄ የወንድ ልጆች ጨዋታ ሲሆን አበባየሁሽ ደግሞ የሴት ልጆች በአዲስ አመት የሚጫወቱት ዜማ ነው፡፡

ምሳሌ 4፡- አበባ አየሁሽ




<u>አበባየሁሽ ግጥም በጥቂቱ</u>

አበባአየሁሽ ለምለም

አበባአየሁሽ ለምለም

ባልእንጀሮቼ ለምለም

ቁሙ በተራ ለምለም

እንጨት ለቅሜ ለምለም

ቤት እስከምሰራ ለምለም

እንኳን ቤትና ለምለም

የለኝም አጥር ለምለም

እቤት አድራለሁ ለምለም

ኮከብ ስቆጥር ለምለም

አደይ የብር ሙዳይ ኮለል በይ፡፡

መልመጃ 4፡- በአካባቢያችሁ የምታውቁትን ህዝባዊ በአል በዜማ ለመምህሩ ዘምራችሁ አሳዩ፡፡

3.1.3 አምልኮ ዜማዎች፡- ቅዳሴ፣ መዝሙር፣ አዛን፣ መንዙማ…ወዘተ ናቸው፡፡ (ይህ የሙዚቃ አይነት ሰዎች ከፈጣሪያቸው ጋር ባላቸው ሃይማኖታዊ ግንኙነት ላይ ብቻ የተመሰረተ የዜማ አይነት ነው፡፡) የቅዱስ ያሬድ ዝማሬ እንደዋና ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡

መልመጃ 5፡- ተማሪዎች የምታውቁትን ሃይማኖታዊ ዝማሬ ለመምህራችሁና ለጓደኞቻችሁ ዘምሩላቸው፡፡

3.1.4 ለስራ የሚዜሙ ዜማዎች፡- የደቦ ዜማ የሚባለው የአንድ አካባቢ ሰዎች በጋራ ሳይደክሙ ስራ ለመስራት ማነቃቂያ እንዲሆን የሚያዜሙት ዜማ ነው፡፡

3.1.5 ለጦርነት የሚዜሙ ዜማዎች፡- ይህ የሙዚቃ አይነት ለጦርነት ጊዜ ወኔ ለመቀስቀስና ማደፋፈሪያነት የሚያገለግል ነው፡፡ ሽለላ፣ ፉከራ፣ ቀረርቶ በመባል ይታወቃሉ፡፡



ምስል 9፡- ሽለላና ፉከራ

ምሳሌ 4፡- ፉከራና ሽለላ ግጥም

እልም ባለው ጫካ

እልም ባለው ዱር

ሲያጉረመርም ያድራል ከመውዜሩ ጋር፡፡

ጎራወና..... ጎራውና..... ጎራውና.....

አጎንብሶ ቢያየው እርጅና ዳብሶት

ስራው ያንበሳ ነው

ያንሰው ተው በሉት፡፡

ኧረ ጥራኝ ጫካው ኧረ ጥራኝ ዱሩ

ላንተም ይሻልሃል ብቻ ከማደሩ፡፡

መልመጃ 6፡- ከላይ የተቀመጠውን የፉከራና የሽለላ ግጥም ለመምህራቻሁ ፊት ለፊት በመውጣት በእንቅስቃሴም ጭምር አሳዩ፡፡

**3.1.7 ለሃዘን የሚዜም ዜማ፡-** ሰውሲሞት፤ ስለሟች ያለፈ ታሪክ በማስታወስ ለማስተዛዘንና ለማላቀስ የሚቀርብ የዜማ አይነት ነው፡፡ ሙሾ፣ የሃዘን እንጉርጉሮ በመባል ይታወቃል፡፡

## 3.2 አገራዊ ውዝዋዜ

በምዕራፍ አንድ ትምህርታችን ውዝዋዜ ከስሜት የሚመነጭ የእንቅስቃሴ ጥበብ ነው ብለናል፡፡ ዳንስ ወይም ውዝዋዜ በተለያየ የመልክአ ምድራዊ ክልል በተለያየ ባህል የሚገኝ ህዝብ የሚያቀው፣ የሚገለገሉበትና ለተለ የአላማቸው ሲሉ በወጉ የሚከሽኑት ጥበብ ነው፡፡

## የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፦

- አገራዊ የውዝዋዜ አይነቶችን ታውቃላችሁ፡፡
- ባህላዊ ውዝዋዜዎችን ትወዛወዛላችሁ፡፡
- የተለያዩ አይነት ኢትዮጵያዊ ውዝዋዜዎችን ትረዳላችሁ፡፡

ከሰው ልጅ የፈጠራ ውጤቶች ማለትም የስነ-ጥበብ ዘርፎች የተለየ ባህርይ ያለው የጥበባት ዘርፍ ነው፡፡ አገራዊ ውዝዋዜዎች ህዝቦች በሚኖሩበት መልከ አምድራዊ አቀማመጥ እና የማህበረሰቡ አኗኗር ባህል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ይህንንም ያሰኘው ከቦታ ቦታ የውዝዋዜዎች አይነት እና እንቅስቃሴ መለያየት ነው፡፡ በኢትዮጵያ በሚገኙ ብሔረሰቦች ውዝዋዜ በሁለት አይነት መንገድ ይደረጋል፡፡ እነርሱም በሃዘንና በደስታ ጊዜ ነው፡፡

የተለያዩ ባህላዊ ውዝዋዜዎች በሀገራችን ሲታወቁ በማህበረሰቡ እንዲሁም በከተማችን አዲስ አበባ በብዛት ከሚጨፈሩና ከሚዘወተሩ ውዝዋዜዎች መካከል የጉራጊኛ፣ ወላይትኛ፣ አማርኛ፣ ትግርኛና ኦሮምኛ ውዝዋዜ አይነቶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እነዚህ ከላይ የተገለጹት የውዝዋዜ አይነቶች እንደየሚኖሩበት አካባቢ ሁሉ እንቅስቃሴያቸውም ይለያያል፡፡ ይህንንም ከዚህ ቀጥሎ በፎቶ እንመልከት፡-

ፎቶ ኢትዮጵያዊ የውዝዋዜ አይነቶች -----------



ተማሪዎች በቤተሰባችሁ ወይም በአካባቢያችሁ የምታውቁትን ኢትዮጵያዊ የውዝዋዜ አይነት በመለማመድ ለመምህራችሁ እና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## 3.2 በብዝኃ ባህል ላይ ያተኮረ ያለፈውና የአሁን የትያትር ጥበብ

ኢትዮጵያ ከመቶ አስር ሚልዮን በላይ ህዝብ የሚኖርባት እና ከሰማንያ በላይ ብሔረሰብ በእምነት በኃይማኖት ቢለያይም ተሳስቦ፤ ተከባብሮ እና ተፋቅሮ የሚኖርባት አገር ነች፡፡ ማህበረሰቡም እንደየባህሉና እምነቱ የተለያየ የአኗኗር ስልቱም የራሱ የሆኑ መገለጫዎች ዘፈኖችና እንጉርጉሮዎች፣ ድራማዊ ይዘት ያላቸው ጨዋታዎች እና ስነ-ጥበባዊ ስራዎች ደስታቸውንና ብሶታቸውን ምኞትና ፍላጎታቸውን የሚገልፁባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከበሩ በርካታ ሃይማኖታዊ በዓላት ውስጥ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ የሚከበረው ጥምቀት በዓል በብዝኃ ባህል ላይ ያተኮረ በርካታ ኪነ-ጥበባዊ ድርጊቶች የሚፈፀምበት አንዱ በዓል ነው፡፡

በጥምቀት በዓል ዕለት ከሐይማኖታዊ ይዘቶች ጋር ተያይዘው እንዲሁም እንዲያው ለማህበራዊ ጠቀሜታቸው ተብለው ከሚቀርቡ ማህበራዊ ባህላዊ ክዋኔዎች መካከል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

- ይህ በዓል በርካታ ባህላዊ ክዋኔዎች የሚፈፀሙበት በዓል ነው፡፡ ባህላዊ ዘፈኖች በበዓል ጥምቀቱ ላይ የሚገኙት "አክባሪዎች" እና "ተሳታፊዎች" የተለያዩ ባህላዊ ዘፈኖችን ይጫወታሉ፡፡ የአማርኛ (የወሎ፣ የጎጃም፣ የጎንደር፣ የምንጃር...) የኦሮሞዎች (የሸዋ፣ የወለጋ) የትግረኛ፣ ወዘተ ባህላዊ ዘፈኖች መዝሙር እዚህም እዚያም በደመቀ ሁኔታ ይጨፈርባቸዋል፡፡ የተለያዩ አይነት ድራማዊ ይዘት ያላቸው ጨዋታዎች ክዋኔዎች እንዲሁም የተለያዩ ሀይማኖታዊ ስዕሎች ኢትዮጵያዊ የሆኑ ተስለው ለገበያው የሚቀርቡበት ታላቅ በዓል ነው፡፡ ባህል ላይ ያተኮረ የክዋኔና የእይታ ጥበባት የሚፈጸምበት ሀገራዊ ክብረ በዓል ነው፡፡

## 3.3 የድራማ ባህላዊ ገጽታ

ተውኔት የራሱ ባህርያት ያሉት አንድ የስነጹፍ ዘር ሲሆን እንደሌሎቹ የስነ-ፅሁፍ ዘሮች የማህበረሰቡን ልዩ ልዩ ገፅታዎች ያንፀባርቃል፡፡ በምዕራፍ አንድ ትምህርታችን ተውኔት ማለት "ተወነ ተጫወተ" ወይም፣ ተጨዋወተ፣ ተነጋገረ እንደ ማለት ነው፡ በአጠቃላይ ጨዋታ፣ ዘፈን ድርጊትን እና እንቅስቃሴን ያካተተ ነገር ማለታችን ይታወሳል፡፡ ስለዚህ ተውኔት ወይም ድራማ የማህበረሰቡን የአኗኗር፡ የአመጋገብ፡ የአለባበስ እንዲሁም አገር በቀል እውቀቶች ይንፀባረቁበታል፡፡ ከነዚህ አገር በቀል እውቀቶች ወይም ባህላዊ ክዋኔዎች ከሚንፀባረቁባቸው ድርጊቶች መካከል እንቆቅልሽ አንዱ ነው፡፡

- እንቆቅልሽ ልጆች በለጋ እድሜያቸው በጠያቂና በተጠያቂ መካከል የሚደረግ ባህላዊ የሆነ አገር በቀል እውቀት ነው፡፡ በጨዋታው ብዙ ቁም ነገር እና የተለያየ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ጉዳዮች ይንፀባረቁበታል፡፡ ልጆችንም በለጋ እድሚያቸው ብልህ፣ አካባቢያቸውን እንዲያውቁ፣ ስለ እንሰሳትና ተፈጥሮ እንዲረዱ፣ የአስተሳሰብ አድማሳቸው እንዲሰፋ የሚያደርግ፡፡

መልመጃ 1

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን የእንቆቅልሽ ጥያቄዎች መልሱ

1. እንዲህ ቢሉ አትታይ እንዲህ ቢሉ አትታይ
2. ቀይ ዘንዶ ዋሻውስጥ ተጋድሞ
3. የላይኛው ቤት ሳይዘጋ ያድራል
4. ለራሱ ሳይቀምስ የቆረሰውን ያጎርስ
5. ልብስም ጉርስም ትሆን
6. ለማታምነው ፊቷ ምራቅ ነው ቅባቷ
7. ቢወረውሩት ወንዝ የማይሻገር
8. መሰላል ያላት ሰው የማይወጣባት
9. በወዲህ ተራራ በወዲያ ተራራ መሐሉ ጠይም ፈረስ
10. ሺ አይን ያለው አጥንት የለው

## 3.3.1 ታዋቂ ታሪኮች

የትምህርቱ ዝርዝር አላማ፦ ታሪኮች ታውቃላችሁ፡፡

### ሀ. ለማ ጉያ

ሻምበል ለማ ጉያ በምስራቅ ሸዋ ከደብረዘይት ከተማ ሰባት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በምትገኝ ድሎ በምትባል መንደር ነሐሴ 12 ቀን 1921ዓ.ም ተወለዱ፡፡ ሻምበል ለማ ከግብርና ሙያ ተነስተው ወደ ትምህርት ቤት የገቡት በ17 ዓመት ዕድሜያቸው ነበር፡፡ ለተወሰኑ አመታት በትምህርት ላይ ከቆዩ በኋላ በመምህርነት ሙያ ለማገልገል በመሻት ወደ መምህራን ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት ገቡ፡፡ በመምህራን ማሰልጠኛ ብዙም ሳይቆዩ የበለጠ የስራ ፍላጎት ያሳዩበት ወደ ነበረው የውትድርና ሙያ ለመሰማራት ወደ አየር ኃይል ሄደው ገቡ፡፡ በኢትዮጵያ አየር ኃይል ውስጥ ተቀጥረው መስራት የጀመሩት በ1943ዓ.ም ነበር፡፡

ለ25 ዓመታት ካገለገሉ በኋላ በ1968ዓ.ም ጡረታ በመውጣት ቀደም ሲል ያዝለቀቅ ያደርጉት ወደ ነበረው የስዕል ስራ ተሰማሩ፡፡ ሻምበል ለማ ጉያን ከሌሎች ለየት የሚያደርጋቸው ወንድሞቻቸውና ልጆቻቸው እንደሳቸው በስዕል ስራ መሰማራታቸው ነው፡፡ ወንድሞቻቸው ቱሉ ጉያ እና አሰፋ ጉያ፤ ልጆቻቸው ደረጄ ለማ ጉያ፥ ነፃነት ለማ ጉያና ሰላማዊት ለማ ጉያ የሻምበል ለማ ጉያን ፈለግ በመከተል በስዕል ሙያ በርካታ ስራዎችን አበርክተዋል፡፡ ሻምበል ለማ በግልና እንዲሁም ከወንድሞቻቸውና ልጆቻቸው ጋር በጋራ በመሆን በሀገር ውስጥ በአዲስ አበባና ደብረዘይት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ ደግሞ በኤርትራ-አስመራ፣ በናጀርያ-ሌጎስ እና በሴኔጋል-ዳካር ስፍር ቁጥር የሌላቸው አውደ-ርዕዮችን አቅርበዋል፡፡ ደብረዘይት መግቢያ ላይ የአፍሪካ ሙዚየም በሚል ስያሜ በተገነባው ዘወትር ክፍት በሆነው ጋለሪ ከውጭም

ከአገር ውስጥ ጎብኚዎች እየሄዱ ስራዎቻቸውን ይመለከታሉ። ሻምበል ለማ የሚስሉዋቸው ስዕሎች ተፈጥሮን ፍንትው አድርገው የሚያሳዩ እንደሆኑ ባለሙያዎች ይናገራሉ። አድናቆትን ካስገኙላቸው ስራዎች መካከል “የሸክላ ገበያ” እና “የደንከል ልጃገረድ” የተባሉት ስዕሎች ተጠቃሽ ናቸው። ሻምበል ለማ ጉያ ተደናቂነት ባተረፉላቸው ስራዎች በርካታ ሰርተፍኬት እና ልዩ ልዩ ሽልማቶችን ያገኙ ታላቅ የኪነ-ጥበብ ሰው ነበሩ።

## ለ. ጥላሁን ገሰሰ (ድምፃዊ)

ድምፃዊ ጥላሁን ገሰሰ ኢትዮጵያ ውስጥ ተደናቂነትና ተወዳጅነት ካተረፉ አቀንቃኞች  መካከል አንዱ ነው። ጥላሁን ከአባቱ አቶ ገሰሰ ወ/ኪዳን እና ከእናቱ ወ/ሮ ጌጤ ጉርሙ መስከረም 17 ቀን 1933ዓ.ም በአዲስ አበባ ተወለደ። ጥላሁን ወደ ሙዚቃው አለም የገባው በ1948ዓ.ም ገና በ15 አመቱ ነበር። በአጭር ጊዜም ታዋቂነትን ለማግኘት የበቃ ትልቅ ድምፃዊ ነው። በሐገር ፍቅር፣  በክቡር ዘበኛና በመጨረሻም በብሔራዊ ትያትር ቤት እየተዘዋወረ ለረጅም አመታት አገልግሏል። ጥላሁን ገሰሰ ከ170 በላይ ዘፈኖችን ያቀነቀነ እና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች በመዝፈን በህዝብ ዘንድ አድናቆትን ያተረፈ ድምፃዊ ነው። ጥላሁን በአማርኛ እና በኦሮምኛ ቋንቋዎች ያቀነቀነ ሲሆን በህይወት ዘመኑ ላበረከተው አስተዋፅኦ በስነ-ጥበባትና  መገናኛ ብዙሃን ሽልማት ድርጅት ተመርጦ ተሸልሟል። ስለ ህይወት ታሪኩ የሚነግር መፅሐፍ “የኢትዮጵያ የሙዚቃ ንጉስ” በሚል ተዘጋጅቶ ለገበያ በቅቷል። ጥላሁን ገሰሰ በሙዚቃው ዘርፍ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረከተ ታላቅ የኪነ-ጥበብ ባለሙያ ነበር።

መልመጃ 2

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልሱ

1. የአርቲስት ሻምበል ለማ ጉያ ተወዳጅነት ያተረፉላቸውን የስዕል ስራዎች ግለፁ
2. ድምፃዊ ጥላሁን ገሰሰ ማቀንቀን የጀመረው በስንት አመቱ ነበር

## 3.4 በብዝሀ ባህል ላይ ያተኮረ ያለፈውና የአሁን የዕይታ ጥበብ

**የትምህርቱ ዝርዝር  አላማ፦**

ተማሪዎች ይህን ንዑስ ርዕስ ከተማራችሁ በኋላ፦

- ብዝሀ ባህል ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ
- የዕይታ ጥበባት በብዝሀ ባህል ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ ታውቃላችሁ
- በድሮ እና በአሁን ጊዜ የሚገኙ ብዝሀ ባህል ላይ ያተኮሩ የዕይታ ጥበባትን ታወዳድራላችሁ
- የቀለማትን ምድብ እና ባህሪያት ታውቃላችሁ
- ቀለማት በተለያዩ ማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን የተለያዩ ትርጉሞች ታውቃላችሁ

የቆየ ታሪክና ባህል ባለው ማህበረሰብ ውስጥ የዕይታ ጥበባት ታሪክን እና ባህልን በማስተዋወቅ ትልቅ ሚና አላቸው። ሀገራችን ኢትዮጵያ ብዝሀ ባህል ያላቸው ህዝቦች የሚኖሩባት ቀደምት ሀገር እንደመሆኗ ብዝሀ ባህል ላይ ያተኮሩ ብዙ የዕይታ ጥበባት ይገኙባታል። እነዚህ የዕይታ ጥበባት በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የአኗኗር ስርዓት ውስጥ እናገኛቸዋለን።

ከእነዚህ የዕይታ ጥበባት ውጤቶች መካከል አልባሳት፣ ጌጣጌጥ፣ የቤት አሰራር ፣ እደ ጥበባት እንዲሁም መዋቢያ መንገዶች ይገኙበታል።

አልባሳት ባህልን መግለጫ መንገዶች ከሆኑት ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው። እነዚህ አልባሳት የአንድን ማህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ተሳቢ ተደርገው የሚሰሩ ናቸው። እነዚህን አልባሳትን በቀደምት ጊዜ የሚያዘጋጇቸው ሰዎች በአካባቢያቸው የሚያገኟቸውን ተፈጥሯዊ ግብአቶችን በመጠቀም የራሳቸውን ልዩ የሆነ የአሰራር መንገድ በመከተል ባህላቸውን ለመጠበቅ እና ለማስፋፋት ችለዋል። እነዚህ አልባሳት በአሁን ጊዜ በብዛት ዘመናዊ የሆኑ መንገዶችን በመጠቀም የተሰሩ እና የሚያተኩሩትም በይበልጥ አሁን ባለው የማህበረሰብ እና ባህል ሁኔታ ላይ ነው። የባህል አልባሳት የምንላቸው በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ ባአላትን እና ዝግጅቶችን ብቻ በመጠበቅ የምንለብሳቸው ሲሆን በድሮ ጊዜ ግን የአዘቦት አልባሳት ነበሩ።



የድሮ የባህል ልብስ



የአሁን የባህል ልብስ

ከአልባሳት በተጨማሪ ባህል ተኮር የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ውስጥ ባህላዊ የቤት አሰራሮች ተጠቃሽ ናቸው።በሀገራችን የሚገኙ የተለያዩ ብሄረሰቦች ባህላቸውን እና የሚኖሩበትን መልክዓ ምድር ታሳቢ ያደረጉ የቤት አሰራር ዓይነቶች አሏቸው። እነዚህ የቤት አሰራር መንገዶች በጊዜ ሂደት ቀድሞ ከነበሩት የአሰራር መንገድ እና ዘዴ እየተለወጡና ዘመናዊነትን

በውስጣቸው እየያዙ መጥተዋል፡፡ በፊት ይሰሩ የነበሩት የቤት አይነቶች ተፈጥሯዊ ግብዓትን በዋናነት ይጠቀሙ የነበሩ ሲሆን ከጊዜ በኋላ ግን እነዚህ ተፈጥሯዊ የሆኑ ግብዓቶች በፋብሪካ ውጤቶች ሊለወጡ ችለዋል፡፡ በፊት የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም ስዕል በመሳል የቤታቸውን ውስጥና ውጭ ያስውቡ ነበር፡፡ አሁን ግን እነዚህ ስዕሎች ዘመናዊ በሆኑ የህትመት ውጤቶች ተቀይረዋል፡፡





በባህል ውስጥ ሌላው ከፍተኛ ቦታን የሚይዙት ጌጣጌጥና መዋቢያዎች ከባህልና ሀይማኖት ጋር ቀጥተኛ ትስስር ያላቸው ናቸው፡፡ በድሮ ጊዜ የሚሰሩባቸው ግብዓቶችም ተፈጥሯዊ የሆኑ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ በድሮ ጊዜ የሚዘወተሩ ጌጣጌጦች መካከል አምባር፣ አሸንክታብ፣ ዶቃ ፣ ቀለበት የመሳሰሉት በስፋት ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር፡፡ በድሮ ጊዜ ለመዋቢያነት ሲውሉ ከነበሩ ነገሮች ውስጥ ደግሞ ንቅሳት፣ እንሶስላ፣ ሰውነት ላይ የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም የሚሳሉ ስዕሎች ይገኙበታል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ከላይ የጠቀስናቸው ዓይነት ጌጣጌጦች እና የመዋቢያ መንገዶች ቢኖሩም የሚሰሩበት መንገድ እና የሚሰጡት ትርጉም ግን ከበፊቱ የተለየ ነው፡፡




ጥ

የድሮ የእጅ ጌጥ(አምባር)

መልመጃ 3

1. ባለፈው እና በአሁን ጊዜ ያሉትን የባህላዊ አልባሳት ልዩነቶች ዘርዝሩ።

2. በሀገራችን ከሚገኙ ባህላዊ የቤት አሰራሮች ውስጥ አንዱን በስዕል ሰርታችሁ አሳዩ።

### 3.4.1 የቀለም ባህላዊ ገፅታ

የአንድ ማህበረሰብ ባህል የራሱ የሆነ ልዩ ልዩ ገፅታዎች ሲኖሩት እነዚህ ገፅታዎች የተለያዩ የስነ-ጥበብ መሰረታዊያንን በውስጣቸው ይይዛሉ ከእነዚህ የስነ-ጥበብ መሰረታዊያን ውስጥ ቀለማት በዋናነት ተጠቃሽ ናቸው። በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የቀለማትን ምንነት እንዲሁም ቀለማት በማህበረሰብ ባህል ውስጥ ያላቸውን ባህሪ እና ጠቀሜታ እናያለን።

### ቀለም ምንድን ነው?

ቀለም ማለት በዐይናችን የምንመለከተው የተለያየ የመታየት አቅም ባላቸው የብርሃን ሞገዶች አማካኝነት የሚፈጠር ነው። ቀለማትን ብርሃን በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ማየት እና መለየት አይቻልም። ቀለማት በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ እነሱም፦

## 3.0.2 የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት፡

የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት የሚባሉት በተፈጥሮ ማለትም ቀለምን ከቀለም ቀላቅለን የማናገኛቸው ሲሆኑ እነዚህ ቀለማትም ቢጫ፣ ሰማያዊ እና ቀይ ናቸው፡፡እነዚህን የመጀመሪያ ቀለማት በአንድ ላይ ስንቀላቅላቸው ቡኒ ቀለም ይሰጡናል፡፡



ሥዕል 1



ሥዕል 2

**3.4.3 ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት፡** ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት የምንላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማትን እርስበእርስ በማቀላቀል የምናገኛቸው ሲሆኑ እነዚህም ቀለማት

1. ሠማያዊ + ቢጫ = አረንጓዴ



2. ቀይ + ሠማያዊ = ወይን ጠጅ



3. ቢጫ + ቀይ = ብርቱካናማ ናቸው፡፡



**3.4.4 ገለልተኛ ቀለማት፡-** ገለልተኛ ቀለማት የምንላቸው በውስጣቸው አንድ የብርሃን ሞገድን ብቻ የማያንፀባርቁ ናቸው። ገለልተኛ ቀለማት የሚባሉት ጥቁር፣ ነጭ እና ግራጫ ናቸው።

ቀለማትን ሞቃት እና ቀዝቃዛ በማለት በሁለት ምድብ እንመድባቸዋለን። ሞቃት ቀለማት የሚባሉት ቢጫ፣ ቀይ እና ብርቱካናማ ናቸው። ሞቃት ቀለማት ቀዝቃዛ ከሆኑት ቀለማት ቀድመው ለዐይናችን የመታየት አቅም ያላቸው ሲሆን እነዚህን ቀለማት በብዛት ታዋቂ የሆኑ የንግድ ምልክቶች ላይ እናያቸዋለን። ቀዝቃዛ ቀለማት የሚባሉት ሠማያዊ፣ ወይን ጠጅ እና አረንጓዴ ናቸው። ቀዝቃዛ ቀለማት ለዐይናችን በተረጋጋ ሁኔታ የምናያቸው እና የተረጋጋ ስሜት እንዲሰማን የሚያደርጉ ሲሆኑ የሚያንፀባርቁት የብርሃን ሞገድ ከሞቃት ቀለማት ያነሰ ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው ቀለማት በሰው ልጅ አዕምሮ ላይ ከፍተኛ ስነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ አላቸው። ቀለማት በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን ይወክላሉ። ቀለማት በተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ዘንድ ያላቸው ትርጉም እና ጠቀሜታም የተለያየ ነው። ለምሳሌ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የደስታ መግለጫ የሆነው ቀለም በሌላው ማህበረሰብ ውስጥ ደግሞ የሀዘን መግለጫ ሊሆን ይችላል።

በሀገራችንም ቀለማት የተለያዩ ውክልናን የሚያገኙበት ስርዓቶች አሉ። ከእነዚህም ስርዓቶች መካከል የደስታ፣ የበዓላት እና የ ሀዘን ስርዓቶችን ማየት እንችላለን። ከሀገራችን አንፃር በደስታ ጊዜ በብዛት ነጭ ቀለም ያላቸው አልባሳት የሚዘወተሩ ሲሆን በሀዘን ወቅት ደግሞ ጥቁር ቀለም ያላቸው አልባሳት ይዘወተራሉ።

ከአልባሳት በተጨማሪ ቀለማት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ መግባቢያነትም በስፋት ያገለግላሉ። ይህም ማለት ቀለማትን ብቻ በመጠቀም መልእክትን ማስተላለፍ ይቻላል።

የቀለማትን አገልግሎቶች ልናይ ከምንችልባቸው ቦታዎች መካከል ከዚህ በታችህ የተጠቀሱትን እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን።

- የትራፊክ መብራቶች



ሰንደቅ አላማዎች



- የትራንስፖርት አገልግሎት መስጫዎች









የህክምና ተቋማት



የንግድ ቦታዎች

## መልመጃ 1

1.ቀዝቃዛ ወይም ሞቃት ቀለማትን ብቻ በመጠቀም ስዕል ሰርታችሁ አሳዩ።
2.ቀዝቃዛ እና ሞቃት ቀለማትን አንድ ላይ በመጠቀም ስዕል ሰርታችሁ አሳዩ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የሃገራችንን ባህላዊ ሙዚቃዎች በተለያየ ጊዜ የምንገለገልበትን ለማየት ተሞክሯል። እነዚህም የሃገራችን ባህላዊ ሙዚቃዎች የማንነታችን መገለጫዎች በመሆናቸው ሁላችንም ልናውቃቸው ይገባል። እንደአስፈላጊነቱና እንደወቅቱ ልንተገብራቸው እና ልንገለገልባቸው ይገባል።

የዕይታ ጥበባት ባህልን ለማስፋፋት፣ ለማስተዋወቅ እና ጠብቆ ለማቆየት ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው።በኢትዮጵያ በሚገኙ የተለያዩ ብሄረሰቦች ባህል ውስጥ የዕይታ ጥበባት በብዛት ተተግብረዋል።በአንድ ባህል ውስጥ የዕይታ ጥበባት ከሚስተዋልባቸው ውስጥ አልባሳት እና ባህላዊ የቤት አሰራሮች ተጠቃሽ ናቸው።ቀለማት በብርሃን ሞገዶች መንፀባረቅ አማካኝነት የሚገኙ ናቸው።በማህበረሰብ ባህል ውስጥ ቀለማት የተለያየ ምሳሌ እንዲሁም የሚወክሏቸው ነገሮች አሏቸው።ቀለማት በአንድ ማህበረሰብ ባህል ውስጥ እንደመግባቢያነት ያገለግላሉ።

## የማጠቃለያ ምዘና

1.<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክለኛውን መልስ አክብቡ</u>

1. ከሚከተለው ውስጥ የደስታ ሙዚቃ የትኛው ነው?
   - ሀ. ሽለላ
   - ለ. ሙሾ
   - ሐ. ሰርግ
   - መ. ሁሉም
2. አሸንዳ አሸንድዬ የጦርነት ባህሎች ናቸው።
   - ሀ. እውነት
   - ለ. ሃሰት
   - ሐ. ሀ ና ለ
   - መ. መልሱ አልተሰጠም
3. ከሚከተሉት ውሰጥ በወንድ ልጆች የሚዜም ዜማ የቱ ነው?
   - ሀ. አሸንዳ
   - ለ. ቡሄ
   - ሐ. አበባየሁሽ
   - መ. ሁሉም
4. በጦርነት ወቅት ለማደፋፈርና ወኔ ለመቀስቀስ የሚያገለግለው የቱ ነው?

ሀ. ሙሾ    ሐ. ፉከራ

ለ. ጨምበላላ    መ. ሰርግ

5. የአምልኮ ዜማ ከሚከተሉት ውሰጥ የቱ ነው?

ሀ. ቅዳሴ    ሐ. የሃዘን እንጉርጉሮ

ለ. አዛን    መ. ሀ ና ለ መልስ ናቸው፡፡

ፀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል የሆኑትን "እውነት" ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፡፡

______________1. ብዝሀ ባህል ማለት ጥቂት ባህሎች ብቻ የሚገኙበት ማለት ነው፡፡

______________2. የዕይታ ጥበባት ታሪክን እና ባህልን ለማስተዋወቅ ትልቅ ጠቀሜታ አላቸው፡፡

______________3. ጌጣጌጥና መዋቢያዎች በባህል ውስጥ ከፍተኛ ቦታን ይይዛሉ፡፡

______________4. የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማትን ቀለምን ከቀለም በማቀላቀል ማግኘት እንችላለን፡፡

______________5. በሀገራችን ቀለማት የተለያዩ ውክልናን የሚያገኙባቸው ባህሎች ይገኛሉ፡፡

______________6. ቀለማት በሰው ልጅ ስነ-ልቦና ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖን ማሳደር ይችላሉ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## ሥነ-ውበታዊ እሴት (ዋጋ)

ማድነቅ

መግቢያ

ስነ-ውበት ጥበብ ነው፡፡ ይህም ጥበብ በርካታ ሙያዎችን በማካተት ጠለቅ ያለ እውቀትንና ማስተዋልን የሚፈልግ የሰው ልጅ የአዕምሮ ውጤት ነው፡፡ በዚህም በሙዚቃ፣ በውዝዋዜ፣ በትያትርና በዕይታ ጥበብ አማካኝነት የሚተላለፍ የጥበብ ዘርፍ ነው፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ የምናገኛቸውን ጥበባት ለሃገራችን ያላቸውን ዋጋ መረዳት እንድንችል በዚህ መዕራፍ እንመለከታለን፡፡

### አጥጋቢ የመማር ውጤት

- የአገራዊ ጥባባትን (በኢትዮጵያ የሚገኙትን የሙዚቃ ጥበባትን) በዝማሬ ታደንቃላችሁ፡፡
- የአካባቢውን ጥበብ በመዝሙር ታቀርባላችሁ፡፡
- ስነ-ውበታዊ እሴቶችን ታውቃላችሁ፡፡
- ባህላዊ የክወናና የእይታ ጥበባትን  ትረዳላችሁ፡፡

## 4.1 የኢትዮጵያ ባህላዊ ሙዚቃን ማድነቅ

ኢትዮጵያ ሃገራችን የብዙ ባህል ባለቤት ነች፡፡ እነዚህም የተለያዩ ባህሎቻችን ከህዝቦች ጋር ለብዙ ዘመናት አብረው የቆዩ ናቸው፡፡ እነዚህን የባህል ክዋኔዎችንና የጥበብ ስራዎችን አስቀድሞ በማየት፣ በማዳመጥ፣ በማንበብና በሌሎች ስሜት ህዋሳቶቸችን በመጠቀም መገንዘብና ማድነቅ ተገቢ ነው፡፡ በተገቢው ሁኔታ ለማድነቅ ፍላጎትና ተነሳሽነት መኖርአስፈላጊ ነው፡፡

ከዚህ ትምህርት በኋላ የሚጠበቁ ዝርዝር ውጤቶች፡-

- በኢትዮጵያ የሚገኙትን አገራዊ የሙዚቃ ጥበባትን በዝማሬ ታደንቃላቸው፡፡
- የአካባቢውን ጥበብ በመዝሙር ታቀርባላችሁ፡፡

ኢትዮጵያ እንዳሏት ብሄር ብሔረሰቦች ብዛት፤ የባህላዊ ሙዚቃ ጥበቧም እንደዚሁ እጅግ በርካታ ነው፡፡ እነዚህም ባህሎች ብርቅና ድንቅ መሆናቸውን መገንዘብ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ከነዚህም ባህሎቿ ሙዚቃ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡
ከዚህ አንጻር ተማሪዎች በአካባቢያችሁ እንዲሁም በመገናኛ ብዙኋን የምታውቋቸውን የባህል ሙዚቃዎች በደንብ በማዳመጥ እንድትመረምሩ ያስፈልጋል፡፡

- የኢትዮጵያ ባህላዊ ክዋኔዎች ሃይማኖታዊ ይዘት ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም ይችላል፡፡

የሀገራችንን የባህል ሙዚቃ ከምናደንቅባቸው ምክንያቶች ውስጥ ሚከተሉትን መጥቀስ እንችላለን፡፡

### 4.1.1 ለብዙ ዘመናት ከውጭ ሀገር ተፅእኖ ስር ያልወደቀ መሆኑ

በርካታ የአለማችን ሃገራት በአውሮፓውያን ቅኝ በመገዛታቸው ምክንያት የሙዚቃ ባህላቸውም ሆነ የሙዚቃ መሳሪያዎቻቸው አውሮፓውያንን ባህሪ የያዘ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ግን በጀግኖች አባቶቻችን ደምና አጥንት ዳር ድንበሯን በማስከበራቸውና ቅኝ ገዢዎችን አሳፍረው በመመለሳቸው የውጭ ተፅእኖ ሙሉ በሙሉ ሊያርፍብን አልቻለም፡፡

? መልመጃ 1፡-የምታውቁትን ጀግኖች አባቶቻችንን ታሪክ ለመምህራችሁ ንገሯቸው፡፡

### 4.1.2 በተለያዩ አካባቢ ብዙ አይነት የሙዚቃ ባህል መኖራቸው

በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በምእራብ እንዲሁም በመካከለኛው ኢተዮጵያ ያሉት የሙዚቃ ባህሎች በምት፣ በድምፅ አደራደር (ቅኝት)፣ በሙዚቃ መሳሪያ፣ በውዝዋዜ፣ በአለባበስ…ወዘተ አንድነትም ልዩነትም አላቸው፡፡

### 4.1.3 በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች መኖራቸው

ከዚህ በታች ተዘረዘሩት ሙዚቃ መሳሪያዎች በሌላ ሃገር ቢኖሩ

እንኳን በአሰራርና በአጨዋወት ኢትዮጵያውያን ለየት ይላሉ፡፡

- ማሲንቆ፣ ክራር፣ ዋሽንት፣ የ ተለያዩ አይነት ከበሮዎች፣ እምቢልታ፣ ነጋሪት፣ ፅናፅል፣ በገና፣ ዲታ(የወላይታ ክራር)፣ መለከት፣… ወዘተ በምሳሌነት ማንሳት እንችላለን፡፡

? መልመጃ 2፡- የምታውቁትን የባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ ለመምህራችሁ ንገሩ፡፡

### 4.1.4 ለተለያዩ አላማዎች መዜማቸው

- ለሃማኖታዊ ክብረ በአላት የሚዜሙ ዜማዎች
- ለባህላዊ ክብረ በአላት የሚዜሙ ዜማዎች
- ለደስታ፣ ለሃዘን፣ ለጦርነት፣ ለፍቅር፣ ለህፃናት የሚዜሙ ዜማዎች

### 4.1.5 ከማህበረሰቡ ጋር ጥብቅ ትስስርና ቁርኝት ያለው መሆኑ

ሙዚቃ ከኢትዮጵያውያን ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ ለዚህም ማስረጃነት ማንኛውም ክንውናችን ከሙዚቃ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ የትኛውም አይነት ድግስ ቢኖር፣ ልደት፣ ሰርግ፣ ግብዣ፣ ክብረ በአል፣ ጦርነት፣ ሃዘን፣ የጋራ ስራ ቢኖር፣ ልጆች ቢሰበሰቡ፣ መንፈሳዊ ጉዳዮች ቢኖረን …ወዘተ ከሙዚቃ ውጭ የማይታሰቡ ናቸው፡፡

? መልመጃ 3፡- በአካባቢያችሁ የምታውቁትን ማንኛውንም አይነት ዜማ ለመምህራችሁ ዘምራችሁ አሳዩ፡፡

### 4.1.6 ለሃገራችን ኢትዮጵያ ከሌሎች ሃገሮች እንደመለያ አርማ የሚያገለግል መሆኑ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በአለም ላይ ከምትታወቅበት ነገር አንዱ የባህል ሙዚቃና ውዝዋዜ ናቸው፡፡ በመሆኑም ሙዚቃ ስልተ ምት፣ ውዝዋዜው፣ አልባሳቱ በአንድ ላይ ኢትዮጵያዊነት መለያን ያጎናፅፋሉ፡፡

በመሆኑም አንድ የውጭ ሀገር ዜጋ እነዚህን የሙዚቃ ስልተ-ምት በማዳመጥና ውዝዋዜውንና አልባሳቱን በማየት ኢትዮጵያዊ መሆናችንን ይለያሉ ማለት ነው፡፡

መልመጃ 4፡- ቀጥሎ የተቀመጡትን ኖታና ግጥሞች በማጣመር ዘምሩ፡፡

የሚቀጥለው የዜማ ግጥም ሃገርን ከወራሪዎች ለመታደግ ከሚቀርቡ ስንኞች ውስጥ የተወሰኑትን እንደምሳሌ ማየት እንችላለን፡፡

በሚቀጥለው ግጥም ውስጥ ኢተዮጵያዊነትንና ጀግንነትን በሩብ ኖታና በግማሽ ኖታ ስለተዋቀረ ግጥሙን ከኖታው ጋር አስማምታችሁ ተለማመዱ፡፡

ኢትዮጵያዊ ጀግና

የማይበገረው፤

እንኳን ለሀገሩ ይተርፋል ለሌላው፡፡
ስጋዬንም ብሉ
አጥንቴንም እንኩ፤
ነገር ግን ሃገሬን አትዮጵያን አትንኩ፡፡
(ግጥም፡- የህዝብ)


ኢ ትዮ ጵያ ዊ ጀ ግ ና
ስ ጋ ዬ ን ም ብ ሉ
የ ማ ይ በ ገ ረ ው
አ ጥን ቴ ንም እ ን ኩ
እ ንኳን ለ ሀ ገ ሩ
ነ ዝ ግ ን ኢ ት
ይ ተ ርፋል ለ ሌ ላ ው
ዮ ጵ ያ ን አ ትን ኩ

❓ መልመጃ 5፡- ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የታዳጊ ልጆች ዜማ ግጥሙን እያነበባችሁ ዘምሩ ከማዜማችሁ በፊት ሙዚቃውን አዳምጡት።

የግጥሙና ዜማ ርዕስ፡- እምዬ ኢትዮጵያ (ከኢትዮጵያ ልጆች የተወሰደ)

እናቴ ኢትዮጵያ ክብርና ኩራቴ

እድለኛነት ነው ባንቺ መጠራቴ።

የሊቃውንት ምድር

ባለብዙ ሚስጥር።

የሰው ልጅ መገኛ

በእምነት መዳኛ።

እናቴ ኢትዮጵያ ክብርና ኩራቴ

እድለኛነት ነው ባነቺ መጠራቴ።

ከጥንት መሰረትሽ

በቅኝ ያልተገዛሽ

በታሪክ ባህልሽ

አብዝተሽ የታደልሽ

በመዝሙር በዜማ

ብክሩናን ያገኘሽ

በፊደል በቁጥር

መለያ የተሰጠሽ።

እምዬ ኢትዮጵያ ኩራቴ ክብሬ ነሽ

እምዬ ኢትዮጵያ ኩራቴ ክብሬ ነሽ።

**መልመጃ 6፡-** የእጅጋየሁ ሽባባው አንድ ኢትዮጵያ የሚለውን ዜማ መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሰረት ተለማመዱ፡፡ በዚህም ዜማ ውስጥ ከመዝፈን ባሻገር ስለኢትዮጵያ ሃገራችሁ ግንዛቤያችሁን ታሳድጋላችሁ፡፡

## 4.2 የኢትዮጵያ ባህላዊ የውዝዋዜ ጥበብ

ውዝዋዜ የአንድ ማህበረሰብ ስነ-ውበታዊ መገለጫ ተደርገው ከሚወሰዱ ኪነ-ጥበባዊ ድርጊቶች መካከል አንዱ ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ ከሰማንያ በላይ ብሔረሰብ ያላት ትልቅ እና የስልጣኔ መገለጫ ከሆኑ ቀደምት አገራት አንዷ ነች፡፡

### ዝርዝር አጥጋቢ የማስተማር ውጤት

- በጋራ ጨዋታ ውዝዋዜን ታቀርባላችሁ፡፡
- የተለያዩ አይነት የውዝዋዜ ምንጮችን ታውቃላችሁ፡፡

ውዝዋዜ እንደ ፈለቀበትና እንደሚነገርበት አካባቢ ባህል የተለያዩ መልኮች አሉት፡፡ ባንድ ቋንቋና ባህልም እንኳን ቢሆን የተለያዩ የውዝዋዜ ስልቶች ሊገኙ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፡- ወላይትኛ፣ ጉራጊኛ፣ ጎጃምኛ፣ ጎንደርኛ ወዘተ------፡፡



ጉራጊኛ ባህላዊ ውዝዋዜ



የሶማሌ ባህላዊ ውዝዋዜ



የአማራ ባህላዊ ውዝዋዜ



የኦሮሞ ባህላዊ ውዝዋዜ



የትግርኛ ባህላዊ ውዝዋዜ



የወላይትኛ ባህላዊ ውዝዋዜ

ውዝዋዜ እንደ የባህሉ አይነት ይለያያል፡፡ ለምሳሌ የቀረርቶና የፉከራ ክዋኔ፡ ከሙሾ ወይም ከሰርግ ጭፈራ ጋር አንድ አይደለም፡፡ ቀረርቶ የሚያሰማው ሰው ከወዲያ ወዲህ እየተንጎራደደ እና ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎችን እያደረገ አይኑን እያጉረጠረጠ፣ ጦር እየሰበቀ ጋሻ አመካከትን እያሳየ ነው የሚከውነው፡፡

ስለዚህ ውዝዋዜ በሀዘንም በደስታም ማህበረሰቡ ስሜቱን የሚገልጽበት፣ የሚዝናናበት፣ የሚደሰትበትና የሚጽናናበት አንዱ የክዋኔ ጥበብ ነው፡፡

**መልመጃ 1፦** <u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን እውነት ወይም ስህተት የሆነውን ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ።</u>

1. ባህላዊ ውዝዋዜ አንድ ማህበረሰብ ስሜቱን የሚገልጽበት የክዋኔ ጥበብ ነው።

2. ባህላዊ ውዝዋዜ ከቦታ ቦታ የተለየ መልክ እና እንቅስቃሴ ሊኖረው ይችላል።

3. የቀረርቶ እና የፉከራ ክዋኔ ከሰርግ ጭፈራ ጋር አንድ ነው።

## 4.3 የኢትዮጵያ ባህላዊ ትያትርን ማድነቅ

ኢትዮጵያዊ የሆኑ ልናውቃቸውና ልናደንቃቸው ከሚገቡ ሥነ-ውበታዊ እሴቶቻችን እንደ ተረቶች፡ የአምልኮ ዝማሬዎች ወይም ዜማ እና ኢትዮጵያዊ ስዕል፣ቅኔ፣እንጉገርጉሮ፣የሙሾ ግጥሞች፣በክብረ በዓላት፣በሰርግ እና በልጆች ጨዋታ፡ የሚዘፈኑ ባህላዊ ዘፈኖች እና ውዝዋዜዎቻችን እንዲሁም ምሳሌያዊ አነጋገሮች፡ ወጎች፡ ቀልዶች፡ ፉከራ፡ ቀረርቶ፡ ሽለላ እና ግጥሞች ሌሎችም የክወናና ዕይታ ጥበባት ውጤቶች የሆኑ ስነ-ውበታዊ እሴቶቻችን ናቸው። እነዚህ የአገር በቀል እወቀቶች እሴቶቻችንን ስለሆኑ ልናደንቃቸውና እና ልናውቃቸው ይገባል።

### ዝርዝር አጥጋቢ የመማር ውጤት

- በሚና ጨዋታ፡ ስዕል በመሳልና በዝማሬ ትሰራላችሁ
- ስለ ባህላዊ የክዋኔና የዕይታ ጥበባት ልዩነት ታውቃላችሁ

### 4.3.1 የኢትዮጵያ ባህላዊ የክወና ጥበባት

**ኪነ-ጥበባዊ መገለጫ ያላቸው፦**

በከብት ስምሪት ጊዜ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች፣ በቀብር ስነስርዓትና ሀዘን ላይ የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞች፣ በክብረበዓላት፣ በሰርግ፣ ልጆች ጨዋታ ላይ የሚዘፈኑ ባህላዊ ዘፈኖች እና ውዝዋዜዎች፣ በደቦ፣ በእድር፣ በእቁብና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ላይ የሚሰነዘሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ሰዎች በሚገናኙባቸው አጋጣሚዎች የሚነገሩ ወጎች፣ ቀልዶች፣ ለማህበረሰቡ ጀግኖች እና ተደናቂ ግለሰቦች የሚነገሩ ግጥሞችና አፈታሪኮች፣ ሌሎችም የክወና ዕይታ ጥበባት ድርጊቶች ማህበረሰቦቹ ስለራሳቸው፣ ስለሰው ልጅ፣ ስለአካባቢያቸውና ባህላቸው እንዲሁም ባጠቃላይ ስለ አገር ያሏቸውን አመለካከቶች የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ድራማዊ ይዘት ያላቸው ጨዋታዎችን በማስመሰልና ድምፅ በማሰማት ለጓደኖቻችሁ በማሳየት እንዲመልሱ አድርጉ፡፡

- የቤት እንስሳዎችን፡ የዱር አውሬዎች የአውሬዎች ድምፅ፤
- መኪና ወይም ብስክሌት መንዳት፤
- ፈረስ ወይም በቅሎ መጋለብ፤
- ልብስ መልበስና እና ማውለቅ፤
- ደስታንና ቅሬታን መግለፅ፤
- እንደአሞራ መብረር እንደ ውሃና እሳት እንቅስቃሴዎችን ማሳየት፡

### መልመጃ ፦ አጭር ድራማ ልምምድ

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን አጭር ድራማ እናት፡ አባት፡ እህት እና ሌባው ልጅ በመሆን ለአራት ሆናችሁ በመለማመድ ለጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

## 4.3.2 እኔ ነኝ ውሮ

አንድ በገጠር ውስጥ ከቤተሰቦቹ ጋር የሚኖር የ14 ዓመት ልጅ ማታ ማታ መብራት ሲጠፋ ከተኛበት እየተነሳ እናቱ ያስቀመጡትን ወተት እየሰረቀ ይጠጣል፡፡ እናትም ሌባው ልጃቸው መሆኑን ቢረዱትም ቢናገሩ አባቱ ይገድለዋል ብለው ስለሚሰጉ ዛሬም ወተቱን ድመቷ ጠጥታው አደረች እያሉ በደላቸውን ለቤተሰብ ያሰማሉ፡፡

አንድ ቀን ሌሊት እንደተለመደው ይሄ ልጅ ሁሉም ተኝቷል ብሎ በገመተበት ሰዓት ተነስቶ ሲያንጎዳጉድ

አባት ይነቁና፡ ማን ነው? ይላሉ፡፡

ልጁም ድመት ለመምሰል ሚያው--- ይላል፡፡

አባት ከራስጌያቸው ያለውን ባትሪ ሊያበሩ ሰበብ የተፈጠረባት ድመት ከግርጌ መተኛቷን ያረጋግጣሉ፡፡ ያለጥርጥር ጓዳውን የሚያንጎዳጉደው ሰው መሆኑን የተረዱት አባት ከመኝታቸው ተነስተው ወደ ልጁ እያበሩ

ማን ነህ አንተ--  ሲሉ በቁጣ ጠየቁ፡፡

ተጋለጥኩኝ ብሎ የሰጋው ልጅም መጀመሪያ ድመቷን ለመምሰል ሚያው--- ካለ ቡኃላ እኔ ውሮ ነኝ... ሲል መልስ ሰጠ፡፡

በዚህ አባት፡ እናት እና የሌባው ልጃቸው ታላቅ እህት ተነስተው ጨለማን ተገን እያደረገ ወተት ሲደፋ የኖረውን ሌባ ያዙ፡፡ ወዲያው ምን እናድርገው.. ሲሉ መከሩ፡፡

አባት ሙልጭ አድርጌ ልግረፈው ሲሉ እህት ተስማማች፡፡ እናት ግን መግረፍ ሌብነቱን ቢያብሰው እንጂ ስለማያስቀረው ሌላ መፍትሄ ይፈለግለት.. አሉ፡ ፡ቀጠል አደረጉና ዳግመኛ ወተት በዞረበት እንዳይዞር ከተፈለገ ሰሞኑን ያተራቀምኩት ወተት ስላለ አንድ ግራሬ ሙሉ በግድ ይጋት፡፡ በጠጣው ወተት ላይ ሌላ ወተት እንዲጠጣ መገደዱ ትልቅ ቅጣት ነው በማለት አስረዱ፡፡ በሃሳቡም ሁሉም ተስማሙና ልጁ እንዳይታገላቸው ሁለት እጆቹ ከምሶሶ ጋር የፊጥኝ ታስረው በትልቅ ግራሬ የተሞላ ወተት ቀርቦ መጋት ሲጀምር ያልቃል፡፡

## 4.4 የኢትዮጵያ ባህላዊ የዕይታ ጥበብ

ሀገራችን ኢትዮጵያ በአለም ላይ ቀደምት ስልጣኔ ካላቸው ሀገራት አንዷ ናት፡፡ በውስጧም ብዙ ባህላዊ የእይታ ጥበባት ውጤቶች የሆኑትን ማለትም የቀለም ቅብ፣ ቅርጻቅርጽ፣ ኪነ-ህንጻ እና እደ ጥበባት በስፋት ይገኙበታል፡፡ በዚህም ምዕራፍ እነዚህ የእይታ ጥበባት በሚገባ እናውቃለን እንዲሁም እናደንቃለን፡፡

### የትምህርቱ ዝርዝር አላማ

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራቹ በኋላ

- የኢትዮጵያን ባህላዊ የእይታ ጥበባትን ምንነት ታውቃላችሁ
- የተለያዩ ባህላዊ የእይታ ጥበባት አይነቶች ማለትም ቀለም ቅብ፣ ቅርፃቅርጽ፣ ኪነ-ህንጻ እና እደ ጥበባትን ታውቃልችሁ
- እነዚህን ባህላዊ የእይታ ጥበባት ማድነቅ ትችላላችሁ

በሀገራችን ብዛት ያላቸው የዕይታ ጥበባት ይገኛሉ:: ከአራተኛው እስከ ሃያኛው ክፍለ ዘመን የተሰሩትን የዕይታ ጥበባት በሁለት ከፍለን ማየት እንችላለን:: የመጀመሪያው ክፍል ውስጥ የሚገኙት የዕይታ ጥበባት፥ ዘመናዊ የዕይታ ጥበብ በሃገራችን መስራት ሳይጀምር በፊት በአብዛኛው በቤተ ክህነት አካባቢ ሲሰሩ የነበሩትን ኀይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ስራዎች ነው ከእነዚህ የዕይታ ጥበባት ውስጥ ሰፊውን ስፍራ የሚይዙት ደግሞ ሐይማኖታዊ የቀለም ቅብ ስራዎች ናቸው:: በሁለተኛው ክፍል የምናገኛቸው ደግሞ በማህበረሰብ ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ የዕይታ ጥበባትን እንደ ሽመና፣ የሸክላ ስራ፣ የጌጣጌጥ ስራዎች ሲሰሩበት የነበረውን ነው:: ወደ እነዚህ ባህላዊ የእይታ ጥበባት ለሀገራችን ያላቸው ጠቀሜታ እጅግ የላቀ ነው:: በመቅጠል በሀገራችን ያሉን ባህላዊ የዕይታ ጥበባት እናያለን::

### 4.4.1 ቀለም ቅብ

የቀለም ቅብ ስራ በሃገራችን ከሚገኙ ቀደምት ባህላዊ የእይታ ጥበባት አንዱና ዋነኛው ነው:: ይህ የጥበብ አይነት ለረጅም ዘመናት በተለያዩ መንገዶች ሲሰራ የነበረ:: በዋነኛነት ይሰራ የነበረው ግን በቤተ ክህነት አካባቢ ሲሆን በውስጡ የሚይዘው ደግሞ ሃይማኖታዊ መልዕክቶችን የሚያንጸባርቁ የመጽሃፍ ቅዱስ ታሪኮችና ሌሎች ሃይማኖታዊ ገድሎችን በተጨማሪም የነገስታት ታሪኮች ላይ ያተኩራሉ:: እነዚህን የቀለም ቅብ ስራዎች የሚሰሯቸው በየገዳሙ የሚገኙ መነኮሳት ናቸው:: እነዚህ የቀለም ቅብ ስራዎች ይሰሩ የነበሩት ስነ ውበታዊ ጠቀሜታን ከመስጠት ይልቅ ሃይማኖታዊ አገልግሎትን ለመስጠት ታስበው ሲሆን የሚሰሩትን ስዕሎች ስንመለከትም አንድን መልዕክት ለተመልካቹ በቀጥታ ለማሳየት የተሰሩ ናቸው:: እነዚህ ቀለም ቅብ ስራዎች በውስጣቸዉ የተለያዩ ጽሁፎችንም ይይዙ ነበር::

 

በኋለኛው ዘመን የተሰሩት የቀለም ቅብ ስራዎች ደግሞ ጭብጣቸውን ከመንፈሳዊ ታሪኮች ጎን ለጎን ዓለማዊ የሆኑትን የነገስታትን እና ቤተሰቦቻቸውን የእለት ተለት ክንዉኖች ፣ ታሪኮች፣ ገድሎች ላይ ያተኮሩ ነበሩ::

 

እነዚህ ባህላዊ የእይታ ጥበባትን ለማዘጋጀት የሚገለገሉባቸውን ግብዓቶች የሚያዘጋጁት በአከባቢያቸው በሚያገኟቸው የተፈጥሮ ውጤቶች ነው:: ተፍቆ እና ተለስልሶ በተዘጋጀ የፍየል ቆዳ (ብራና) እና ለቀለማቱ ደግሞ ከአፈር፣ ከቅጠላቅጠል እና የተለያዩ የእንስሳት ተዋፅዖ ይጠቀሙ ነበር:: እንዲሁም ሌሎች ማዋሃጃ እና ማጣበቂያዎችን በማዘጋጀት ይሰሯቸው ነበር::

## 4.4.2 ኪነ-ሕንፃ

ኢትዮጵያ የቀደምት ስልጣኔ ባለቤት እንደመሆኗ የተለያዩ ስልጣኔ የሚገልፁ የኪነ ሕንፃ ጥበባት ይገኙባታል፡፡ እነዚህ የኪነ ሕንፃ ጥበባት በብዛት የሀይማኖት ቦታዎች እና በቤተ መንግስታት ላይ እንመለከታቸዋለን፡፡ የሀይማኖት ስፍራዎች በብዛት አንድ ወጥ ድንጋይ በመፈልፈል ወይም ድንጋዮችን በመጥረብ ይሰሩ ነበር፡፡ በተጨማሪም በእንጨት እና በጭቃ የተሰሩ ባህላዊ እና ታሪካዊ የኪነ ሕንፃ ውጤቶች ይገኛሉ፡፡ በቤተ መንግስታት የምናየው የኪነ ሕንፃ ጥበብ ደግሞ ድንጋዮችን በመደርደር እና ተፈጥሯዊ የሆኑ የመለሰኛ መንገዶችን በመጠቀም ይሰሩ ነበር፡፡ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው የኪነ ሕንፃ ጥበባት በሙሉ የተሰሩት ዘመናዊ የመስሪያ ማሽኖችን ሳይጠቀሙ በሰው ሃይል ብቻ ነው፡፡



ላሊበላ ውቅር አብያተ-ክርስትያን



የፋሲለደስ ቤተ-መንግስት



አል ነጃሺ መስጊድ

### 4.4.3 የዕደ ጥበብ እና የጌጣጌጥ ውጤቶች

ሀገራችን ኢትዮጵያ የብዙ ብሄረሰቦች መኖሪያ እንዲሁም የብዝሃ ባህል መገኛ መሆኗ ይታወቃል:: እነዚህ ልዩ ልዩ ታሪክ እና ባሕል ያላቸው ብሄረሰቦች የባህላቸው መገለጫ የሆኑ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ የዕደጥበብ ውጤቶችን እንዲሁም ትውፊቶቻቸውን የምናይባቸው የጌጣጌጥ ስራዎች አሏቸው:: ከእደጥበብ ውጠቶች ውስጥ ተፈጥሯዊ ግብዓቶችን ብቻ በመጠቀም ይሚሰሩትን እንደ ሽመና፣ የሸክላ ስራዎች፣ የሠፌድ ስራዎች እንዲሁም ልዩ ልዩ የቅርጫት ስራዎች ይገኙበታል:: በሀገራችን የሚገኙትን ጌጣጌጦች ስንመለከት እንደሚገኙበት ማህበረሰብ እና አካባቢ ያላቸውም ትርጉም እና ጌጣጌጦቹ የሚደረጉባቸው የዕድሜ ክልል የተለያየ ነው:: እነዚህ የጌጣ ጌጥ ስራዎችን ለመስራት እንደ ወርቅ፣ ብር፣ ነሃስ፣ ጨሌ፣ ዛጎል እንዲሁም የተለያዩ ብረታብረቶችን ይጠቀማሉ::

የዕደ ጥበብ ስራዎች





ጌጣጌጦች





❓ መልመጃ፦ 1የምታደንቁትን ሀገር በቀል የዕይታ ጥበብ በስዕል ሰርታችሁ አሳዩ።

2 ከአገር በቀል የዕይታ ጥበባት ውስጥ የምታደንቁትን መርጣችሁ የምታደንቁበትን ምክንያት ግለፁ።

## ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ የኢትዮጵያን ሙዚቃ የምናደንቅባቸውን ጥቂት ምክንያቶችን አይተናል። በተጨማሪም የሃገራችን ባህላዊ መሳሪያዎችን እንደዚሁ በጥቂቱ አይተናል። የሃገራችን ሙዚቃ የሚለይበትን ትንሽ ምክንያት አይተናል። የተቀመጡትንም መዝሙራት ብንለማመዳቸው ቅኝቶችን ከማስገንዘብ በላይ ሃገራዊ ፍቅርና አንድነትን ትረዱበታላችሁ።

በሀገራችን ብዙ የዕይታ ጥበባት ውጤቶች ይገኛሉ። በቀደመው ጊዜ በሃገራችን ሲሰሩ የነበሩት የቀለም ቅብ ስራዎች በአብዛኛው በአብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም አቢያተ መንግስታት አካባቢ ይሰራሉ። በኢትዮጵያ የነበሩት የኪነ ህንፃ ጥበባት ታሪካዊ ይዘት ያላቸው እና ወጥ ድንጋይን በመፈልፈል እንዲሁም ዲንጋዮችን ጠርቦ በመደርደር ይሰሩ ነበር። በኢትዮጵያ የሚገኙ ብሄረሰቦች የሚያጌጡባቸው ልዩ ልዩ ጌጣጌጦች የራሳቸው መገለጫ ያላቸው እንዲሁም በተለያየ የዕድሜ እርከን የሚደረጉ ናቸው።

## ማጠቃለያ ምዘና

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ካነበባችሁ በኋላ ትክክል የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልሱ።

1 ኢትዮጵያውያን ከሌሎች ሀገር ዜጎች የዜማ ስልት የራሳቸውሙዚቃ በመስማት ብቻ መለየት ይችላሉ። __________

2. የሀገራችን ሙዚቃ ከኢትዮጵያውያን ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው። __________

3. ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የሚገኙ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሉም። __________

4. ሙዚቃን ለበርካታ አላማ በማዋል እንጥቀምበታለን። __________

5. በነጭ ቅኝ ገዢ በመገዛታችን ሙዚቃችን የውጭ ተጽዕኖ አለበት። __________

6. በሀገራችን ከሚሰሩ የዕይታ ጥበባት ውስጥ ሰፊውን ስፍራ የሚይዘው ጌጣ ጌጦች ናቸው። __________

7. በኢትዮጵያ የሚገኙት ታሪካዊ ኪነ ሕንፃዎች ከአንድ ወጥ ድንጋይ ተፈልፍለው ብቻ ነው የተሰሩት። __________

8. በሀገራች ያሉ ቀደምት የለቀለም ቅብ ስራዎች ሀይማኖት ላይ ያተኩሩ ነበሩ።

9.ባህላዊ ጌጣጌጦች ከወርቅ፣ ብር ፣ ጨሌ ፣ ዛጎል የመሳሰሉትን በመጠቀም ይሰራሉ። __________

10.ታሪካዊ ቀለም ቅብ ስራዎችን ለመስራት የተለያዩ የፋብሪካ ኬሚካሎችን ይጠቀሙ ነበር። __________

# ምዕራፍ አምስት

## ጥመርታ ዝምድናና፣ትግበራ

### የቡድን ስራ

### መግቢያ

የክወናና የዕይታ ጥበባት ብቻውን የሚቆም ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም ትምህርቶች ጋር ከፍተኛ ቁርኝትና ትስስር ያለው በመሆኑ ይሄንን ዝምድና በሙዚቃ፣ በውዝዋዜ፣ በትያትር እና በእይታ ጥበባት ያለውን ተዛምዶ እንመለከታለን፡፡ ይህንንም ትስስር በዜማ በውዝዋዜ በድራማና ጭውውት እንዲሁም በስነ ስዕል ጥበብ በማዋሃድ እንረዳለን፡፡

### አጠቃላይ አላማ

- የአካባቢውን ጥበብ በመዝሙር ታቀርባላቸሁ፡፡
- የአካባቢውን ጥበብ በሚና ጨዋታ ታቀርባላችሁ፡፡
- የአካባቢውን ጥበብ በውዝዋዜ ታቀርባላችሁ፡፡
- የአገራዊ ጥበባትን (በኢትዮጵያ የሚገኙትን የክወናና የእይታ ጥበባትን) በዝማሬ፣ በውዝዋዜ፣ በሚና ጨዋታ፣ በሥዕልና በፍቶግራፍ የተሰሩት ስራዎችን ታደንቃላችሁ፡፡

አንድ ሰው ብቻውን ወይም ከሌሎች ጋር በአንድነት ሙዚቃን ሊጫወት ይችላል። በግል ክህሎትን ለማዳበር መለማመድ ተገቢ ቢሆንም ከሌሎች ጋር አብሮ መስራት የራስን ችሎታ ከማሳደግ ባለፈ ያለንን እውቀት ለሌሎች እንድናስተላልፍ ያስችለናል። በቡድን መስራት ከአንድ ግለሰብ ባለፈ ለሌሎችም እንድናስብ ስለሚያደርገን የማህበራዊ ኑሮ ክህሎታችንን እናዳብርበታለን።

ተማሪዎች ይህንን ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ

- ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለውን ዝምድና ትረዳላችሁ።
- በምታውቁትን መዝሙር መልእክቱንና ዝምድናውን ትገልፃላችሁ።

## 5.1 ሙዚቃን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

ሙዚቃ በባህሪው የማነቃቃትና ማዝናናት ባህሪ ስላለው ሌሎች የትምህርት አይነቶችንም በዜማ ማዋሃድ  ጥሩ ውጤት ያስገኛል።

ሙዚቃ ከሃሳብ ትምህርት ጋር፡- የሙዚቃ ኖታ የሂሳብ ስሌትን የሚጠቀም በመሆኑ የሂሳብ ትምህርት ባህሪያትን በሙዚቃ ውስጥ እናገኘዋል።

ምሳሌ፡-

- ✓ አራት ሩብ ኖታ እኩል ይሆናል አንድ ሙሉ ኖታ፡፡ (የመደመር ባህሪ)
- ✓ ግማሽ ኖታ እኩል ይሆናል ሁለት ሩብ ኖታ፡፡ (የማካፈል ባህሪ)
- ✓ ሙሉ ኖታ እኩል ይሆናል ሙሉ ኖታ እረፍት፡፡ (አቻ እኩልነት ባህሪ)

መልመጃ 1፡- የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ

1. አንድ ሩብ ኖታ አቻ እረፍት ኖታ ምንድን ነው? -----------
2. ሁለት ግማሽ ኖታ ስንት ሩብ ኖታ ይሰጠናል? -------------
3. አንድ ሙሉ ኖታ ስንት ግማሽ ኖታ ይወጣዋል? ------------

### 5.1.1 የሙዚቃ ትምህርት ከአካባቢ ሳይንስ ጋር፡- የሙዚቃ

ትምህርት ከአካባቢ ሳይንስ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት አለው፡፡

- ✓ ድምፅ በእርግብግቦሽ የሚፈጠር ነው፡፡ ይህንንም የሚያጠናው ሳይንስ ነው፡፡
- ✓ የሙዚቃ መሳሪያዎች በዋነኝነት ከተፈጥሮ ውጤቶች የሚሰሩ ናቸው፡፡
- ✓ ድምፅ ተፈጠሯዊ በመሆኑ የሙዚቃ ድምፆችም እንዲሁ የተፈጥሮ ውጤት ናቸው፡፡
- ✓ አካባቢያችንን ራሱ ዜማ አለው፡፡ (ወንዞች፣ ጫካ፣ የወፎች ዝማሬ፣ እንስሳት ድምፅ፣ የሰዎች ሁካታ ወዘተ፡፡ በጥልቀት ካደመጥነው መሳጭ ድምጾች ናቸው፡፡

መልመጃ 2፡- የሚከተሉት ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ ስጡ

1. የሙዚቃ መሳሪያ በአካባቢያችን በምን በምን ሊሰራ ይችላል?
2. በአካባቢያችሁ የምታውቁትን የእንስሳትን ወይም የተፈጥሮ ድምፅ አስመስሉ?

### 5.1.2. ሙዚቃ ከቋንቋ ትምህርቶች ጋር፡- ሙዚቃ ከቋንቋ ትምህርቶች ጋር ዝምድና አለው፡፡

- ✓ ሙዚቃ ዜማ በውስጡ ግጥሞችንና ቃላቶችን የያዘ በመሆኑ ቋንቋ ላይ ያለንን ግንዛቤና እውቀት ያዳብርልናል፡፡
- ✓ ሙዚቃን በመስማት የማዳመጥ ችሎታን፣ በመዘመር የመናገር ችሎታን፣ ዜማና ግጥም በመፃፍ የመጻፍና ማስተዋል ችሎታን እናዳብርበታለን፡፡

### 5.1.3. ሙዚቃ ከኤሌክትሮኒክስና ኤሌክትሪሲቲ ጋር፡- ሙዚቃ ከኤሌክትሮኒክስና ኤሌክትሪሲቲ ጋር ከፍተኛ ዝምድና አለው፡፡

- ✓ የሙዚቃ ማጫወቻዎች፣ የሙዚቃ ድምፅ ማጉያዎች፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ጭምር የኤሌክትሮኒክስ ውጤት ናቸው፡፡ በመሆኑም ለቴክኖሎጂ የሚኖረንን ግንዛቤ እናሳድግበታለን፡፡

### 5.1.4 ለእርስ በራስ ግንነኙነት፡- ሙዚቃ የአንድን ትምህርት ቤት ተማሪዎች እርስ በራስ የሚኖራቸውን ግንኙነት እንዲሁም ከመምህራኖቻቸውና ከአስተዳደሩ ጋር ተግባቦታቸውን ያሻሽላል፡፡ በዚህም ጥሩ መማር ማስተማር ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

መልምጃ 3፡- ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ተግባራዊ ምላሽ ስጡ

1. በቤታችሁ ከምትሰሙት ማንኛውም አይነት ሙዚቃ የተወሰነውን ግጥሙን ፅፋችሁ ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡
2. በቤታችሁ የምታዳምጡትን ሙዚቃ (ዜማ) ድምፁን በማስመሰል ተለማመዱ፡፡
3. በምታውቁት ዜማ የራሳችሁን አዲስ ግጥም በማስገባት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

### 5.1.5 ሙዚቃ ከታሪክ ትምህርት ጋር፡- ሙዚቃ ከታሪክ ትምህርት ጋር ጥብቅ ግንኙነት አለው፡፡

✓ ታሪክ ነጋሪ ሙዚቃ ቀደም ሲል የነበሩት ሰዎች ያደረጓቸውን ድርጊት፣ ሁኔታ የሚገልፅ ግጥም ያለው ሙዚቃ ማለት ነው፡፡

✓ ታሪክ በሙዚቃ ተቀምሮ ሊቀመጥና ከትውልድ ወደትውልድ ሊሸጋገር ይችላል፡፡

✓ ሙዚቃም የራሱ ታሪካዊ አመጣጥ ያለው መሆኑ

✓ ታሪክ በሙዚቃ ሲነገር በቀላሉ የማይረሳ፣ ስሜትን ቀስቃሽ መሆኑ …ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡

መልመጃ 4፡- ለሚከተሉት ጥያቄዎች ተግባራዊ ምላሽ ስጡ

1. ከምታውቁት ታሪክ ነጋሪ ሙዚቃ አንዱን ለመምህራቸሁ መርጣችሁ ዘምሩ፡፡
2. ተማሪዎች ለክፍላችሁ ይሆናል የምትሉትን አንድ ዜማ ሁላችሁም በመስማማት ትመርጡና ለክፍላችሁ መለያ ይሆናችሁ ዘንድ በቀን በቀን በጋራ ዘምሩት፡፡ የመረጣችሁትን ዜማ ለክፍላችሁ እንደ አርማ (መለያ) እንዲሆናችሁ በስፖርታዊ ውድድርና በሌሎችም ክፍላችሁ በሚኖረው ተሳትፎ በጋራ ዘምሩት፡፡

## የመልመጃ መዝሙር 1፡- ርዕስ፡- ልምምድ




### ልምምድ

ሙዚቃ የሚወድ ያጨብጭብ ችብችብ፤

ሙዚቃ የሚወድ ያጨብጭብ ችብችብ፡፡

ሙዚቃ የሚወድ ይደንስ  ዳንስ ዳንስ፤

ሙዚቃ የሚወድ ይደንስ  ዳንስ ዳንስ፡፡

ሂሳብን የሚወድ ይደምር ችብችብ፤

ሂሳብን የሚወድ ይቀንስ ችብችብ፡፡

ሂሳብን የሚወድ ያባዛ ችብችብ፤

ሂሳብን የሚወድ ያካፍል ችብችብ፡፡

ቋንቋንም የሚወድ ያዳምጥ ችብችብ፤

ቋንቋንም የሚወድ ይናገር ችብችብ፡፡

ቋንቋንም የሚወድ ያንብብ ችብችብ፤

ቋንቋንም የሚወድ ይፃፍ ችብችብ፡፡

### የመልመጃ የመዝሙር 2፡- ርዕስ ፡- እንነሳ በጥዋት

ዶሮ ጮኸ በጥዋቱ፤

እንነሳ እንሁን ብርቱ፡፡

ያልነቃ ሰው ጠዋት ቀድሞ፤

ብርቱ አይሆንም ፈፅሞ፡፡

እንነሳ በማለዳ፤

ልብስ እንልበስ ጥርስ እናፅዳ፡፡

እንዘጋጅ በደስታ፤

ለስንፍና አንስጥ ቦታ፡፡




**?** **መልመጃ 5፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በፅሁፍ መልሱ

1. ከላይ የቀረበው መዝሙር ስለምን እንደሚናገር ግለፁ፡፡
2. ከዚህ መዝሙር ምን ትምህርት እንዳገኛችሁበት ግለፁ፡፡

## 5.2 የውዝዋዜ ጥበብ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

ውዝዋዜ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በተለይም ከሰውነት ማጎልበቻ ትምህርት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ ከሌሎች የትምህርት ዘርፎች

ጋር በቀጥታ ባይሆንም በተዘዋዋሪ ለትምህርቶቹ ተማሪዎች ለሚኖራቸው አቀባበል የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም፡፡ ውዝዋዜ ክዋኔ ጥበብ እንደመሆኑ የአካል እንቅስቃሴን የሚጠይቅ ዘርፍ ነው፡፡ ለዚህም ውዝዋዜ በምናደርግበት ጊዜ ሙሉ ሰውነታችን ስለሚንቀሳቀስ ከውዝዋዜው ባለፈ ጤነኛ የሆነ የሰውነት አቋም እና የአተነፋፈስ ስርአት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ይሄ ደግሞ ለማንኛውም የትምህርት ዘርፍ የሚያገለግል መሰረታዊ የሆነ የጤና ስርዓት ነው፡፡

## ዝርዝር አጥጋቢ የመማር ውጤት

- ውዝዋዜዎችን ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ዝምድና ታውቃላችሁ
- በጋራ ጨዋታ ከእፀዋት ውዝዋዜን ትመለተከታላቹ፡፡
- የተለያዩ አይነት የእንቅስቃሴ ምንጮችን ታውቃላችሁ

ከዚህ ቀጥሎ የቀረበውን እንቅስቃሴ ደረጃ በደረጃ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ፡- እነዚህ መደበኛ ያልሆኑና ያልተለመዱ እንቅስቃሴዎች ስትሰሩ በተቃራኒው ሊኖራችሁ ስለሚገባ ስለመደበኛና ቀላል የእርምጃ እንቅስቃሴ ምንነት ግንዛቤ ታዳብራላችሁ፡፡

ጉልበት ሳይታጠፍ እጆቻችሁ ቁልቁል ተንጠልጥለው ላለመንቀሳቀስ ድርቅ እንዳሉ፡ አንገታችሁ ቀጥ እንዳለ፡ ወገብም እንዲሁ እንደተገተረ ውጥረት በነገሰበት አይነት እርምጃ አካሄድ በክፍል ውስጥ መንቀሳቀስ፡፡

የሰውነት ክብደታችሁን ሙሉ በሙሉ ተረከዞቻችሁ ላይ በማሳረፍና መላው ሰውነታችሁን ፍጹም ላላ ዘና በማድረግ ለመሬት ስበት ፍጹም ታዛዥ እንዲሆን በማድረግ በዝግታ በክፍላችሁ ውስጥ መንቀሳቀስ፡፡

የሰውነት ክብደታችሁን ሙሉ በሙሉ በፊተኛው የእግራችሁ መዳፍ ጣቶች ላይ በማሳረፍ አይኖቻችሁ በሩቁ አንድ ቦታ ብቻ እንዲያዩ በማድረግ በረጃጅም እርምጃ በክፍል ውስጥ መንቀሳቀስ፡፡

ከዚህ በመቀጠል የቀረበውን የእጸዋት ከተክል ጀምሮ አብቦ እስከ መክሰም ያለውን ሂደት በመከተብ በውዝዋዜ በማቀናጀት አቅርቡ፡፡ ይህንን እንቅስቃሴ በውዝዋዜ በመከተብ ከተፈጥሮ ጋር ያላችሁን ቅርርብ ያዳብርላችኃል፡፡

### 5.2.1 እፅዋትን መግለፅ

በቅድሚያ ሰውነታችሁን በእህል ዘር ፍሬ መስላችሁ አእምሮአችሁን

አሳምኑ፡፡ እናም ያቺ የእህል ዘር ፍሬ ስትበቅል፣ስታድግ፣ስታብብ፣ስትዳብር፣ ስትስፋፋ፣ ጥንካሬ እና ሃይል ስታጎለብት፡ ከፍተኛ የእድገት ደረጃ ላይ ስትደርስ እያሰባችሁ ቆዩ፡፡

ከዚያም ደረጃ በደረጃ የሰውነት ይዘታችሁን እየጨመራችሁ ከመብቀል፣ ከማደግ፣ከመዳበር፣ከመስፋፋት፣ጥንካሬንና ሀይልን እያጎለበታችሁ፣ ከፍተኛ የእደገት ደረጃ ላይ ከመድረስና ከማበብ አንጻር ውስጣዊ ሃይላችሁንና የሰውነት ይዘት እድገታችሁን እስከመጨረሻው ድረስ ከደረሳችሁ ቡኋላ፤ በመቀጠል ደረጃ በደረጃ እየጠወለገና እየሞተ ወደ መሬት እንደሚተኛ አበባ እየሚሸሽ ሲሄድ ያለውን ሂደት በ በእንቅስቃሴ ማስመሰልና መግለጽ ነው፡፡



የእጸዋት እድገት ደረጃ



እጸዋት የእድገት ደረጃቸው ሲያበቃ

## 5.3 የትያትር ጥበብ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና፡-

ትያትር በተለያየ መንገድ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት አለው፡፡ ለምሳሌ ከሳይንስ ትምህርት ጋር በእጅጉ ይዛመዳል ይህም ማለት ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ከአማርኛ ትምህርት ጋር የንባብ ባህልን ከማዳበር እና ስለ ኢትዮጵያ ስነ-ጽሁፍ እና ትያትር ለመገንዘብ በአያሌው ይጠቅማችኃል፡፡ ተማሪዎች ትያትር ጥበብን በምትማሩበት ወቅት በራስ መተማመን ታዳብራላችሁ ፈጣሪ እና ችግር ፈቺ እንድትሆኑ ያደርጋችኃል፡፡

### ዝርዝር አጥጋቢ የማስተማር ውጤት

ከዚህ ትምህርት በኃላ፡-

- የክዋኔ ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለው ዝምድና ትማራላችሁ፡፡
- በሚና ጨዋታ ከዋኔን ከሳይንስ ትምህርት ጋር ያለውን ዝምድና ታውቃላችሁ፡፡
- ድራማዎችን ትሰራላችሁ፡፡

## 5.4 የዕይታ ጥበብ ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው ዝምድና

ይህን ንዑስ ምዕራፍ ከመማራችን በፊት የዕይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ማጣመር ያለውን ጠቀሜታ እንመልከታለን።

የዕይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር ስናጣምር ትምህርቱን ቀላልና አዝናኝ በሆነ መንገድ መረዳት እንችላለን። ትምህርታችንንም በንቃት ኣንድንከታተል እና እንድንረዳ ያደርገናል ። በተጨማሪም ፈጠራ የተሞላበት የችግር አፈታት በላቀ ደረጃ እንድናሳድግ ያስችለናል። የዕይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር መጣመር በትምህርት ውጤታችን ላይም ከፍተኛ የሆነ መሻሻል ያመጣል።

**የትምህርቱ ዝርዝር አላማ**

ተማሪዎች ይህን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የዕይታ ጥበባት ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ማጣመር ያለውን ጠቀሜታ ትረዳላችሁ።
- ከዋክብትን፣ ወንዞችን ፣ አዕዋፋትን ይመሳሰሉትን የተፈጥሮ አካላት በስዕል ታሳያላችሁ።
- የሳይንስ ትምህርት በዕይታ ጥበባት ዕይን መመልከት ትችላላችሁ።

### 5.4.1 የዕይታ ጥበብ ከአካባቢ ሳይንስ አንፃር

የዕይታ ጥበባት ከአካባቢ ሳይንስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው። እንደሚታወቀው በአካባቢያችን እጅግ ብዙ ዓይነት ቀለማት ፣ ቅርፆች ፣ ፎርሞች ያላቸው ተፈጥሯዊ እንዲሁም ሰው ሰራሽ ነገሮች ይገኛሉ።

ከነዚህ በአካባቢያችን ከምናያቸው ተፈጥሯዊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ ከዋክብት፣ ልዩ ልዩ ወንዞች፣ አዕዋፋት፣ ተክሎች የመሳሰሉት ይገኛሉ። እነዚህ ተፈጥሯዊ የሆኑትን ነገሮች ከዕይታ ጥበብ አንፃር በምናይበት ወቅት ስለ ባህሪያቸው ፣ ስላላቸው ገፅታ እንዲሁም ከአካባቢያችን ጋር ያላቸውን መዛመድ ቀላል በሆነ መልኩ መረዳት እንችላለን።

ይህም የአካባቢ ሳይንስ ትምህርታችን ላይ ነገሮችን አዲስ እና አስደሳች በሆነ መንገድ እንድንረዳቸው ያስችለናል።

እንደምሳሌ ብንወስድ አዕዋፋትን የዕይታ ጥበባትን ከሳይንስ የትምህርት ዘርፍ ጋር አጣምረን በምንሰራበት ወቅት የአዕዋፋቱን ዝርያ

በቀለማቸው ፣ በፎርማቸው እንዲሁም በላያቸው ላይ የሚገኙትን ልዩ ልዩ ቅርፆች ያላቸውን ቀለማት መነሻ በማድረግ በቀላሉ መለየት ያስችለናል።



ምስል፡- የተለያዩ አዕዋፋት

በሌላ በኩል ከዋክብትን በስዕል ስራ ለመስራት በምንሞክርበት ወቅት የምንስራቸውን

የከዋክብት ዓይነቶች ፣ መገኛቸውን ብሎም በስርዓተ ህዋ ውስጥ ምን ዓይነት እንቅስቃሴ እንዳላቸው ለማወቅ እድል ይኖረናል።





ምስል፡- የተለያዩ ከዋክብት

ወንዞችን፣ ተራሮችን ፣ እንስሳትን በስዕል በምንሰራበት ወቅት ከአካባቢ ሳይንስ ትምህርት አንፃር በትምህርቱ ውስጥ የሚገኙ ነገሮችን እየሰራን እንደመሆናችን መጠን አካባቢያችንን ለማጤን ፣ ለማወቅ እንዲሁም አካባቢያችንን ከሌላው ጊዜ በተለየ ትኩረት እንድናስተውል ያስችለናል፡፡




ምስል፡- የተለያዩ ወንዞች

ይህም ትምህርቱን ከንባብ በተጨማሪ በተግባር እያየን እና እየሰራን ስለሆነ እንዳንረሳው ይረዳናል፡፡

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ መሰረታዊ የሆኑትን የሙዚቃ መፃፊያ ኖታ ምልክቶችን ሙሉ ኖታ፣ ግማሽ ኖታ፣ ሩብ ኖታ እንዲሁም ሙሉ ኖታ እረፍት፣ ግማሽ ኖታ እረፍት፣ ሩብ ኖታ እረፍት ምልክቶችን አፃፃፍ ከነውክልና ጊዜ ዋጋቸው ለይተናል፡፡ በተጨማሪም እነዚህን ምልክቶች አቆጣጠራቸውን ተለማምደናል፡፡

እንዲሁም የተለያዩ መልመጃ የሚሆኑ ዜማዎችንና መዝሙሮችን ተለማምደናል፡፡ በመሆኑም በዚህ በሦስተኛ ክፍል የጀመርናቸውን የሙዚቃ እውቀቶች እንዳንረሳቸው በግላችን ደጋግመን በእረፍት ጊዜአችን መለማመድ ያስፈልጋል፡፡ ሙዚቃና ሌሎች የጥበብ ክህሎቶች የግል ፍላጎትንና ጥረትን የሚፈልጉ በመሆኑ ሁልጊዜ በግላችን ለማወቅና ለመለወጥ ጥረት አድርጉ፡፡

የዕይታ ጥበባት እና የአካባቢ ሳይንስ ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ከሌሎች የትምህርት አይነቶች ጋር በማጣመር ትምህርቶቹን ቀላልና አዝናኝ በሆነ መንገድ መረዳት እንችላለን፡፡ በአካባቢያችን የምናያቸውን ተፈጥሯዊ የሆኑ ነገሮችን በዕይታ ጥበብ አማካኝነት ማጥናት እና ማበልጸግ እንችላለን፡፡ የዕይታ ጥበባት አካባቢያችንን እንድናስተውል እንድንጠብቅ እና ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ ለመኖር ይረዱናል፡፡

## የማጠቃለያ ምዘና

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል የሆኑትን "እውነት" ትክክል ያልሆኑትን "ሀሰት" በማለት መልሱ።

_______________1. ሙዚቃን መዝሙር በመዘመር መለማመድ አያስፈልግም።

---------------------2. የአካባቢን እንክብካቤ በዜማ መማር እንችላለን።

--------------------3.የሳይንስ ትምህርትን ከዕይታ ጥበባት ጋር በጥምረት መስራት አይጠቅምም።

_______________4. የእይታ ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶች ጋር በምናጣምርበት ወቅት ትምህርቶቹን ቀላል በሆነ መንገድ መረዳት እንችላለን።

_______________5. የዕይታ ጥበባት አካባቢያችንን በትኩረት እንድናይ ይረዱናል።

_______________6. በተፈጥሮ ላይ የምናያቸው ቀለማት ከዕይታ ጥበብ አንፃር ልንጠቀምባቸው አንችልም።

## ዋቢ መፃህፍት

1. ታሪክና ምሳሌ፣ ክቡር ደ/ር ከበደ ሚካኤል (1999 እ.ኢ.አ)
2. የኢትዮጵያ ታሪክ 1847-1983፤ ባህሩ ዘወዴ (1999 እ.ኢ.አ)
3. Ezra Abate, (2009) Ethiopian kinit (scales), Analysis of the formation and structure of the Ethiopian scale system
4. Ashenafi kebede ,( 1971) The music of Ethiopia ;its development and cultural setting
5. Ellinger, J. (2014) Music theory fundamentals
6. Jones, Russel and Cathrine ( 2021) , understanding basic music theory
7. Bahru Zwede ,(2002) The history of modern Ethiopia 1855-1991
8. የኢትዮጵያ ሙዚቃ ታሪክ 1889-1983 ተስፋዬ ለማ (2005 እ.ኢ.አ)
9. The little book of music theory, Amsco Publications, New York.
10. Harmony 1, Barrie Nettles, Berklee collage of music, (1987)

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

2014 ዓ.ም / 2021 /